ናይል
THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


## ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
አቶ እምቢያለ በየነ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ፈታሒ በቃሉ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ:-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
አብነት ሰለሞን
የኑስ ኑሬ

**ግራፊክስና ሌይአውት:-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች:-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች:-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ግርማ ቅባቱ (ዶ/ር)
ይናገር ተ/ስላሴ
መርኃጽድቅ መኮንን
ቻላቸው ታረቀኝ
ምናለ አ.
ታምሩ ከፈለኝ
ቤተልሄም ሃይለማርያም

**ፎቶ አንሺዎች:-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ:-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት:-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች:-**
ንብረት ታፈረ
አለምነሽ ሙሉ



ስልክ:- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# የዩኒቨርሲቲው ቀን በጋራ ጠንክሮ ለመስራት የጥሪ ደውል ነው!

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባሕር ዳር ፖሊ ቴክኒክና የመምህራን ኮሌጅ (ፔዳ) ተጣምረው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሚለውን ስያሜ ያገኘበትን 16ኛ ዓመት ምክንያት በሚያዚያ ወር ለመጀመሪያ ጊዜ የዩኒቨርሲቲውን ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች ማክበሩ ይታወቃል። በዝግጅቱም ላይ ነባር የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞችና ምሩቃን ተገኝተው ስለዩኒቨርሲቲው ያላቸውን ስሜት አካፍለዋል።

የፔዳና የፖሊ ግቢዎች ስራ ሲጀምሩ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው ‹ሀ› ብሎ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ምሁራንን አፈርቷል፤ እያፈራም ነው። ለዚህ ስኬት የሁሉም ማህበረሰብ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። በእነዚህ ረጅም አመታት በርካታ መልካም አፈፃፀሞች ጎልተው የታዩበት ነበር። አሁንም እነዚህን መልካም አፈፃፀሞችን አጎልብቶና ክፍተቶችን በማረም ለቀጣይ ስኬት ርብርብ ማድረግ ወሳኝ ነው።

ዩኒቨርሲቲያችን የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ መሠረት በማድረግ ጥራት፣ አግባብነትና ተደራሽነት ያለው ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ራዕይ ጥበብ 2017ን ለማሳካት ያስቀመጣቸውን ስትራቴጅክ ግቦች በተሟላ ሁኔታ ለማሳካት በየአመቱ በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማሕበረሰብ አገልግሎት፣ በቴክኖሎጂ ስርጸት/ሽግግር እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ዘርፎች ስራውን በስፋት እየሰራ ይገኛል። አበረታች ውጤትም እያስመዘገበ ይገኛል። የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዕውቀት፣ ክህሎትና በአመለካከት ብቁ፣ ተገቢ የሆነ የሰው ኃይል በማፍራት፤ የምርምር ማዕከላትን በማጠናከርና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያተኮሩና ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን በማካሄድ፤ የክልሉን ፍላጐት ማዕከል ያደረገ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራን በማጠናከር በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ፋይዳ ያላቸው የማሕበረሰብ አገልግሎት ስራዎች በማከናወን እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው መልካም አስተዳደር የሰፈነበት፣ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ስራ የሚካሄድበት እንዲሆን በማስቻል የዩኒቨርሲቲውን ታሪክ ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሀላፊነት አለበት።

ዩኒቨርሲቲያችን ወደፊትም ይህን የዩኒቨርሲቲ ቀን በየአመቱ ሲያከብር ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ማለትም አመራሮች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እንዲሁም የቀደሞ የዩኒቨርሲተው ምሩቃን ዩኒቨርሲቲውን በማስተዋወቅና ራዕዩን እውን በማድረግ ረገድ የበኩላችንን መወጣት ይጠበቅብናል። የዩኒቨርሲቲውን ቀን ስናከብር አሁን ላለው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ስላለፈው ታሪክ ትውስታ ለመፍጠርና አሁን የደረስንበትን ስኬት እውቅና ለመስጠት እንዲሁም ለወደፊት የትኩረት አቅጣጫን ለማስቀመጥ በመሆኑ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የጥሪ ደውል ነው - የበለጠ በጋራ ጠንክሮ በመስራት ለስኬት ለመብቃትና ራዕይ 2017ን እውን ለማደርግ የታለመ ደውል!

### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

በናይል ጋዜጣ ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512 በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን።

ዝግጅት ክፍሉ

## ቁልፍ መልዕክት

# የዩኒቨርሲቲያችን ንጽህና በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ንጽህና የአንድ ማህበረሰብ የዕድገት ደረጃ አመልካች መመዘኛ ነው። የግለሰብ፣ የቤተሰብ፣ የማህበረሰብና በአጠቃላይ የሀገር ንጽህና ሁኔታን በማየት የነዋሪዎቹን የአመለካከትና የዕውቀት ደረጃ ማወቅ ይቻላል። በዚህ አጭር ጽሑፍ በንጽህና በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ያሉ አመራሮች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞችና መምህራን ያላችውን አመለካከትና አፈፃፀም እንደሚያሳይ በማቅረብ የተሻለ ንጽህና በዩኒቨርሲቲያችን የሚረጋገጥበት አግባብ ላይ ውይይት እንዲኖር ለማነሳሳት ነው።

ራዕይ ጥበብ 2017 የዩኒቨርሲቲያችን ንጽህናየሚረጋገጠውየዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ የራሳቸውን፣ የቢሯቸውን፣ የሚጠቀሙባቸውን ሌሎች መሠረት ልማቶች ንጽህና መጠበቅ እንደሚገባው ከልብ አመኔታ ሲኖራቸውና በዚሁ ልክ ሲተገበሩ እንደሆነ ያስቀምጣል። በመሆኑም የአንድን አመራር/ሠራተኛ/መምህር ቢሮና የሚጠቀምበትን ሌሎች መሠረት ልማቶች ከንጽህና አኳያ በመመዘን ያለውን የአመለካከት ደረጃና ተግባር ማየት ያስችላል።

የዩኒቨርሲቲያች ንጽህና የሚጀምረው ከግለሰቡና ከሚጠቀምበት ቢሮ ነው። በመሆኑም በግለሰቦች መካከል ባለ የአመለካከትና የመተግበር ልዩነት የአንዱ ቢሮ በስርዓት ነገሮች ተቀምጠውና በንጽህና ተይዘው ሲታዩ በተመሳሳይ ቢሮ ያለ ሌላ ሰው ለመግባት እንኳ በሚያስፈራና ተፀድቶ የማያውቅ እስኪመስል ድረስ ንጽህና የጐደለበት ሁኔታ ይታያል። በተመሳሳይ ሁኔታ በአመራር የአመለካከትና የግንዛቤ ልዩነት ምክንያት አንዳንድ የመማሪያ ክፍሎች በስርዓት ወንበር ተቀምጦባቸውና ንጽህናቸው ተጠብቆ ሲገኙ ሌሎች በእጅጉ የተዘበራረቁ ወንበሮችና በተበጫጨቀ ወረቀት የተሞሉ ሆነው ይታያሉ። በሁለቱ መማሪያ ክፍሎች መካከል ያለው ልዩነት የፀዳውን በአመለካከትና በተግባር የተለወጠ አመራር የመራው መሆኑ ሲሆን ሌላው የቆሸሸውና የተዘበራረቀው መሪ የለሽ በሚመስል ሁኔታ ላይ መሆኑ ነው።

የቤተ-ሙከራዎችንም ንጽህና በምንፈትሽበት ወቅት ተመሳሳይ ልዩነት ይታያል። አንዳንድ ቤተ-ሙከራዎቻችን ወለሉ ሳይቀር ተሰምሮ መቆም የሚቻልበትና የማይቻልበት ተለይቶ እንዲሁም የቤተ-ሙከራ ዕቃዎች በስም ተለይተውና የሚታወቅ አድራሻ ተሰጥቷቸው የሚሠራበት አግባብ መስርተዋል። በተቃራኒው ደግሞ የቤተ-ሙከራ ክፍሉንም ሆነ ዕቃዎችን በሚገባ ያልተደራጁበትና ንጽህና የጐደላቸው መኖራቸውም እውነታ ነው። የእነዚህም ልዩነት በንጽህናና በስርዓት የተቀመጠው በአመለካከቱና ተግባሩ ያደገ አመራር፣ ሠራተኛ፣ መምህርና ተማሪ ያለው ሲሆን በታቃራኒው ንጽህናና ስርዓት የጐደለው መሪውም ሆነ ፈፃሚዎች በአመለካከትና በተግባር ያልዳበሩ መሆናቸው ነው።

የንጽህናን ጉዳይ በግቢም ሆነ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በማሳደግ ረገድ በተመሳሳይ ሁኔታ ሊብራራ ይችላል። በአመለካከትና በተግባር ያልተለወጠ ፕሬዚዳንት ባለበት ዩኒቨርሲቲ ንጽህናን ማረጋገጥ ያስቸግራል። እንዲሁም በየግቢዎቹ ያሉ ከፍተኛ አመራሮችና ፈፃሚዎች ግንዛቤያቸው ሳይገነባ ንጽህናን በእዚያ ግቢ ማረጋገጥ ያስቸግራል።

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እየተገበረ ያለውን ያልተማከለ አስተዳደር መሠረት አድርገን ስናይ ግቢዎች ያሉበት የንጽህናና ስርዓት የመከተል ደረጃ በየግቢዎቹ ያሉ አመራሮች የደረሱበትን የአመለካከትና የተግባር ደረጃ የሚያሳይ ነው። አንድ ግቢ ባልደረቁና በፈኩ አትክልቶች፣ በስርዓትና በቦታቸው በተቀመጡ ወንበሮችና በማይሸቱና ምቹ ሽንት ቤቶች የተሞላ ሆኖ ሲገኝ ሌላው ግቢ ደግሞ እንደ ነገሩ ሆኖ ይታያል። ይህን ልዩነት የምናገኝበት ዋነኛ ምክንያት የአመራር ልዩነት ነው። ከአመራሩ በሚወርድ አግባብ በፈፃሚዎችም ላይ ልዩነት ይኖራል። የፈፃሚዎችን አመለካከትና ተግባር የማስተካከል ጉዳይ ደግሞ የአመራር ስራ ነው።

በንጽህና የተሞላ ግቢ፣ ቢሮ፣ የመማሪያ ክፍል በመፍጠር የመማር ማስተማርና የምርምር ሂደቱን ስኬታማ ማድረግ ይቻላል። በመሆኑም የዩኒቨርሲቲያችን በተለያዩ እርከን ያላችሁ አመራሮች የጥበብ ማማ የሆነች ዩኒቨርሲቲ ለመመስረት በሚደረገው ርብርብ የመሪነት ሚናችሁን በሰርቶ ማሳያ መርህ በመመራት ንጽህናን እናበርክት። መምህራን፣ ተማሪዎችና የአስተዳደር ሠራተኞ በራዕይ ጥበብ 2017 የንጽህና መስመራችንን በመገንዘብ ለስኬታማነቱ ከራሳችን በመጀመር እንስራ።

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

# አበይት ዜናዎች...

## ዩኒቨርሲቲው የተመሰረተበትን ቀን በደመቀ ሁኔታ አከበረ

በሙሉጎጃም አንዱአለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባሕር ዳር ፖሊ ቴክኒክና የመምህራን ኮሌጅ (ፔዳ) ተጣምረው የዩኒቨርሲቲ ስያሜ ያገኙበትን 16ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ለመጀመሪያ ጊዜ የዩኒቨርሲቲውን ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች አከበረ፡፡

መነሻና መድረሻውን ፔዳ ያደረገው የ2008 ዓ.ም እጩ ተመራቂ ተማሪዎች የተካፈሉበት በወንዶች፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ተከፍሎ የተካሄደው የሩጫ ውድድር የመርኃ ግብሩ መክፈቻ ነበር፡፡ ሩጫው በተካሄደበት ወቅት የፖሊስ ማርሽ ባንድ የተለያዩ ጣዕመ ዜማዎችን በማሰማት ለበዓሉ ከፍተኛ ድምቀት በመስጠት ሩጫውን አጅቧል፡፡

የዩኒቨርሲቲውን ታሪክ የሚዘክር ጥናታዊ ፅሁፍ በታሪክ ምሁሩ በዶ/ር ፋንታሁን አየለ የቀረበ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ፖሊ ቴክኒክ ሲመሰረት የመሰረት ድንጋይ ያስቀመጡና የመጀመሪያ ተመራቂዎችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ ከቦታው ተገኝተው ያስመረቁ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ የትምህርት መሳሪያም ሆነ ቢሮ ሣይሟላ ከበርካታ ተግዳሮቶች ጋር ወደ ሥራ መግባቱንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቶ አሁን ካለበት ደረጃ መድረሱን ከቀረበው ፅሁፍ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ዩኒቨርሲቲው ካለፈው ታሪክ ተነስቶ ያከናወናቸውን በርካታ አኩሪ ተግባራትና አሁን የደረሰበትን ደረጃ ገልፀዋል፡፡ የቀድሞ አመሰራረቱ ሲዘከር የእያንዳንዱ ሠራተኛና ትምህርት ክፍል የራሱ የሆነ የተለያየ ታሪክ እንዳለውና አሁን አገሪቱ የምትፈልገውን እድገት እያስመዘገበ ያለ ዩኒቨርሲቲ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ አያይዘውም የበዓሉ መከበር ዋና ዓላማ አሁን ላለው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ስላለፈው ታሪክ ትውስታ ለመፍጠር እንዲሁም ለወደፊት የትኩረት አቅጣጫን ለመለየት ታልሞ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ፣ በጡረታ የተገለሉ አንጋፋ ሠራተኞችና መምህራን እንዲሁም የቀድሞ ተመራቂዎች በበዓሉ ታድመዋል፡፡ በፊት የነበሩትን ተግዳሮቶችና አሁን የሚታየውን ለውጥ በማንሳት ውይይት ተካሂዷል፡፡

በዝግጅቱ ወቅት የሻማ ማብራት፣ የዳቦ ቆረሳ፣ የሙዚቃ ዝግጅት እንዲሁም የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች ተካሂደዋል፡፡ ለበዓሉ ከፍተኛ ድምቀት ያጐናፀፈው ፕሬዚዳንቱን ጨምሮ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች የተሳተፉበት የእግር ኳስ ውድድር ሲሆን የአስተዳደር (ጥበብ) ህንፃ አመራሮች አሸንፈው የዋንጫ ባለቤት ሆነዋል፡፡ ሴት መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ከሴት ተማሪዎች ጋር ባደረጉት ውድድር ተማሪዎች በሰፊ ውጤት አሸንፈዋል፡፡ የዱላ ቅብብል ጨዋታና የጆንያ ውስጥ ሩጫ ውድድሮች ተካሂደው ለበአሉ የበለጠ ድምቀት ሰጥቶታል፡፡

## በዩኒቨርሲቲው የሩዋንዳ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ህዝብ ገለፃ አደረጉ

በታድዬ አስማረ

የአፍሪካ ከፍተኛ መሪዎች የሚሳተፉበት ጣና ፎረም ላይ ለመሳተፍ ወደ ባሕር ዳር ከመጡት መሪዎች መካከል የሩዋንዳ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሉዊስ ሙሽኪያቡ ‘ልማታዊ መንግስት በአፍሪካ’ በሚል ርዕስ የሩዋንዳን ልምድ ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብና ተሳታፊ ለሆኑ የአፍሪካ ከፍተኛ መሪዎች ንግግር አደረጉ፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ አቅራቢዋንና ተሳታፊዎችን አመስግነው በአፍሪካ ሀገራት የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ልምድ ማካፈልና ሀሳብ መለዋወጥ የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ሀላፊነት መሆኑን ገልጸው ህዝበ ገለጻው ዩኒቨርሲቲው ምሁራንንና ባለሙያዎችን በማገናኘት ለአህጉሪቱ የተሻለ ለውጥ እንዲመጣ የሚሰራውን ስራ እንደሚያግዝ ተናግረዋል፡፡

የእለቱ ህዝበ ገለፃ አቅራቢ የተከበሩ ሉዊስ ሙሽኪያቡ እንደገለፁት ሩዋንዳ በአሁኑ ጊዜ የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት በማስፈን ዜጐች በሀገራቸው ያለ ልዩነት እንዲኖሩ፣ ከበቀል የፀዳ የፍትህ ስርዓት በመዘርጋት በፖለቲካው ዜጐች እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ እንዲሁም የሀገሪቱን ዜጎች የኢኮኖሚ ተጠቃሚ በማድረግ በተለይ የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ በወሳኝ የውሳኔ ሰጭነት ቦታ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ተችሏል፡፡ አቅራቢዋ ሩዋንዳ አሁን የደረሰችበትን ደረጃ ለመድረስ የተጎዘችበትን መንገድ በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

የሞዛምቢክ የቀድሞ ፕሬዚዳንት የተከበሩ ሚስተር ጆኩይም ቺሳኖ ገለጻውን የመሩት ሲሆን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ አማካሪና የጣና ፎረም ም/ሊቀ መንበር ፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴ እና ፕሮፌሰር አደባዮ ኦሉኮሺ ገለጻውን ተካፍለዋል፡፡

የአፍሪካ ከፍተኛ መሪዎች፣ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተካፈሉ ሲሆን የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው ከመድረክ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡ የቅድመ ጣና ፎረም ህዝበ ገለፃ በጣና ፎረም ሴክሬታሪያት እና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ትብብር የተዘጋጀ ነው፡፡

## የኢትዮ ሱዳን ቀን ተከበረ

በትዕግስት ዳዊት

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ እና በሱዳን መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር የሚያስችለውን ሁለተኛውን የኢትዮ-ሱዳን ቀን እንዲሁም 3ኛውን የናይል ስምፖዚዬም አከበረ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ መርኃ ግብሩን ሲከፍቱ የኢትዮ-ሱዳን ቀን መከበሩ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የትምህርትና ባህል ልውውጥ የበለጠ እንደሚያጠናክረው ገልፀው እለቱ መከበሩ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና በሱዳን ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የተፈረሙት የአጋርነት ስምምነቶችን የበለጠ በማጠናከር ወደ ተግባር እንዲገባ እንደሚያግዝ ተናግረዋል፡፡

በእለቱ በዩኒቨርሲቲው ምሁራን በዶ/ር ፋንታሁን አየለ እና በአቶ አለሙ አስፋው “Ethio-Sudan Relation through Century” እና “From Independence into Interdependence” በሚሉ ርዕሶች ላይ ጥናታዊ ፅሁፍ ያቀረቡ ሲሆን ከሱዳን ዩኒቨርሲቲዎች የመጡት ዶ/ር ሀቲም ሲገድ “Mutual Historical Relation between Ethiopia and Sudan” እና ዶ/ር ሙሐሙድ Ethio-Sudan cooperation” በሚል ጥናታቸውን አቅርበዋል፡፡

በእለቱ 3ኛው የናይል ስምፖዚዬም “Nile Water Resource for development and cooperation from past to the future” በሚል መሪ ቃል ተካሂዷል፡፡ በእለቱ ከአስር በላይ የሚሆኑ ጥናታዊ ጽሑፎች በምሁራን ቀርበው ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

በመረኃ ግብሩ መክፈቻ ላይ ለእንግዶች በማርሽ ባንድ የታጀበ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል የተደረገ ሲሆን የሁለቱ ሀገራት ብሔራዊ መዝሙሮች ተዘምረዋል፡፡ ከሱዳን በመጡ የሱዳን ባህላዊ የሙዚቃ ባንድ የሱዳን የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃዎች ለታዳሚዎች ቀርበዋል፡፡ በእለቱ ከተለያዩ የሱዳን ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ሃያ ስድስት ምሁራን፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተሳትፈዋል፡፡

## አካዳሚው ሰልጣኞችን አስመረቀ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ማሪታይም አካዳሚ በመካኒካልና በኤሌክትሪካል የትምህርት ዝግጅት ሙያ ያላቸውን ሰልጣኞች ለስድስት ወራት ያህል በመርከበኝነት ሙያ የንድፈ ሀሳብንና የተግባር ትምህርቱን በሚገባ ተከታትለው ያጠናቀቁትን ስልሳ ሁለት ሰልጣኞች በዋናው ግቢ በሚገኘው ማሪታይም አካዳሚ ቅጥር ግቢ ውስጥ አስመረቀ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ለተመራቂዎችና ለቤተሰቦቻቸው የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው የዓለማችን ሶስት አራተኛው ክፍል በውሃ የተሸፈነ በመሆኑና በተለያዩ አህጉራት የሚኖሩ ሕዝቦች ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር የባሕር ላይ ጉዞ ስለሚያስፈልግ ዩኒቨርሲቲው ይህንን በመገንዘብ ከኢትዮጵያ ማሪታይም ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ችሎታውና ፍላጐቱ ያላቸውን ዜጐች አሰልጥኖ ለዓለም ገበያ እያቀረበ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለመርከበኝነት ሙያ ዋናው መመዘኛ ታማኝነት በመሆኑ በሥራው ዓለም ላይ ሲሰማሩ የተለያዩ ተግዳሮቶችን ተቋቁመው ያላቸውን እውቀትና ክህሎት በማዳበር ተወዳዳሪ ሊሆኑ እንደሚገባ ዶ/ር ባይሌ አሳስበዋል፡፡ ተመራቂዎቹ ከሌሎች ሀገራት ዜጐች ጋር ተጋግዞ የመስራት እድሉ ስለሚያጋጥም በመቻቻልና በመከባበር ሥራቸውን በሚገባ እንዲወጡም በአደራ መልክ አሳስበዋል፡፡

ተመራቂዎች በተወካያቸው አማካኝነት ስልጠናውን በአግባቡ እንደወሰዱና ለወደፊት በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን ወደ ተግባር ቀይረው ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ሥራ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን እንዲሁም በስድስት ወር ቆይታቸው ከተሰጡት ትምህርቶች በርካታ እውቀት መገብየታቸውን ገልፀዋል፡፡

በምረቃ ሥነ ስርዓቱ ላይ ለተመራቂ ተማሪዎች የምስክር ወረቀት የተሰጠ ሲሆን በውጤት ብልጫ ላስመዘገቡ ሁለት ሰልጣኞችም ልዩ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡ ተመራቂዎቹ በአማራ ፖሊስ የማርሽ ባንድ በመታጀብ ሙያዊ የሆኑ የተለያዩ የሰልፍ ትርኢቶችን አሳይተዋል፡፡

To follow the latest news about BDU, check out our website:-

**http://www.bdu.edu.et**

facebook page:-

**www.facebook.com/bduethiopia**

# Unfairness in Broad Daylight

**By Yinager Teklesellasie,**

**Department of English Language and Literature**

Nowadays, it has become a culture in many places in Bahir Dar to stand in a queue to take a rickshaw, commonly known as a *Bajaj*, or a taxi wherever one is heading. As a result, it is very common to see long queues of commuters in front of the main gate of *Peda* Campus and in many other places in the city. Some of us join these queues almost every day at different times of the day. I read somewhere that a society which has the culture of standing in a line for getting different services has a very strong sense of fairness. When one joins a line he or she may say: "since you've arrived before me, you deserve to be treated first". This is a simple but respectful show of fairness to your fellow countrymen or countrywomen. However, this sense of fairness is being violated again and again by many *Bajaj* drivers and some commuters in front of the main gate of *Peda* Campus.

As a dweller of the city I almost always join queues twice a day in front of the main gate of *Peda* Campus. Sometimes, particularly on Saturday and Sunday afternoons, I stand in a long queue under a scorching sun and if the number of rickshaws coming to *Peda* Campus is small, then I have to embrace myself for a long wait in the baking sun to go to *Gebeya*. Recently, I have devised two strategies to make life easier for me when I stand in a long line and under a scorching sun. The first one is carrying an umbrella just to fend off the strong sun light. The other one is reading a novel until my turn arrives to get in a *Bajaj*.

If the line is long, I always see injustice being committed in broad day light. I have observed repeatedly that some people, for whatever reason, do not want to join the line and are ready to pay the rickshaw drivers more than the legal fare and take them wherever they want. Since most *Bajaj* drivers know that this is a common practice in front of the main gate of *Peda* Campus, they park their *Bajajs* in front of the gate and wait for people who are going to take them as contract taxis even if there is a long line of commuters waiting for their services. Over the last couple of years I have repeatedly seen people coming from behind me and taking *Bajajs* though I was standing in a long line for a long time. This is the most annoying thing for anyone standing in a long line and under a sweltering sun.

More than once I told the *Bajaj* drivers and the commuters who were taking the *Bajajs* as contract taxis that what they were doing was unfair and that everyone should join the line, and that the commuters who were standing in the line should be served first and foremost. I exchanged angry words with both the drivers and the people who were taking the *Bajajs* as contract taxis. The drivers told me that it was business and that it was their right to give services for anyone who paid them more. And the people who were taking the *Bajajs* as contract taxis told me to mind my own business. I got discouraged and stopped asking those people to do the right thing. The vast majority of the people who stand in the line in front of *Peda* Campus are university students and I am usually surprised by their patience and tolerance of injustice.

If someone has an emergency, they should take a *Bajaj* as a contract taxi even if there is a long line. I think no one has a problem with that, but if people take a *Bajaj* as a contract taxi just to avoid standing in a long line, this is not fair. I feel that some people think that they are too smart or too rich to stand in a line. Recently, a colleague of mine told me, waiting for a *Bajaj* in front of the main gate of *Peda* Campus *that* people who avoid standing in a line and take *Bajajs* by paying more want to show us how powerful they are. I think he is right. These people are telling us that they can do whatever they want because they have more disposable income. Another colleague said to me, again waiting for a Bajaj at the same place, that this is a small sign of a systemic and national problem in which people want to benefit illegally.

**This is the most annoying thing for anyone standing in a long line and under a sweltering sun.**

I think standing in a line to get whatever services is a sign of modernity and of being fair. However, when you see people taking *Bajajs* by paying more while you are standing in a line as a law-abiding citizen, you can't help feeling stupid and helpless. My worst fear is that this unfairness with regard to the use of *Bajajs* in front of the gate of a higher learning institution might be a sign of something bigger and rotten in our society. *Bajaj* drivers who take advantage of the impatience of people who stand in a long line are extortionists and should be dealt with legally and swiftly.

## ህልም እልም

ከገጽ 15 የዞረ

እጅግ የበዛ ማስመሰሏ ለሷ ያላቸውን ግምት ያሳንሰዋል፡፡

ፀሎታቸው ገና ብዙ ይቀረዋል፡፡ እሷም በያንዳንዱ አንቀጽ ማብቂያ ላይ "አሜን" ማለቷን አላቆመችም፡፡ ልቧ ግን ለማንም አሜን ብሎ አያውቅም፡፡ ይሁን ማለት ተሸናፊነት ይመስላታል፡፡ እንቢተኝነትና ተቃውሞ ለሷ የመብለጥ አርማዎቿ ናቸው፡፡ ዳሩ ምን ታድርግ የቀረጿት እጆች እንቢተኛ ስለሆኑ እሺ ማለትን ከማን ትማር፡፡ ከከንፈሮቿ ትህትና ይልቅ የልቧ እብሪተኝነት ጎልቶ ይታያል፡፡

መምሬ ጣሰው የእለቱን ውዳሴ ማርያም ጨርሰው " ይዉድስዋ " እያሉ ነው፡፡

የእምነት ነገር ሲነሳ ሁሌም በልቧ ትስቃለች፡፡ ፍትህ ባያሌው የተወደደበት ፈጣሪ ጌታና ሎሌ አድርጎ እያኖረ ተመስገን ማለት ያሰራሩን አድሎአዊነት መደገፍ ነው፤ ብላ ታስባለች፡፡ "እኔ ያሁሉ ጋሬጣና እሾክ ሲከበኝ ፈጣሪ እረፍት ላይ ነበር እንዴ?" እያለች ትስቃለች፡፡ ቢሆንም አንደበቷ አሜን ማለት አያቆምም፡፡

"ጎንበስ ማለቴን ሰዎች እንጂ ፈጣሪ እንዲያይልኝ አልፈልግም፡፡ ሰዎች እኔን ካመኑኝ የኔ ፈጣሪን ማመን ትርፍ ነገር ነው፡፡" እያሉ መፈላሰፍ የዘወትር ስራዋ ነው፡፡

"በሃሊዮ፣ በነቢር፣ በገቢር የማይሰራ ሀጢያት እግዚያብሄር ይፍታ"

ጎንበስ ብላ ተሳለመች፡፡ ማሰርና መፍታት የጊዜ እንጂ የመምሬ ጣሰው ስልጣን እንዳልሆነ በልቧ እያሰበች፡፡ መምሬ ጣሰው ከፀለዩበት ጣሳ ውስጥ ውሃ በመዳፋቸው እየሰፈሩ ሶስት ጊዜ ፊቷን ከረጯት በኋላ ቤቱን እየዞሩ እረጭተው በድጋሚ አቡነ ዘበሰማያት አድርሰው ከመቀመጫጨው ተመለሱ፡፡

"እሁሁሁሁሁሁሁሁ. . . ተመስገን . . . ተመስገን ጨለማውን አሳልፈህ ብርሃን የምታሳየን አምላክ . . . ተመስገን"

"አይ አባ. . .የጨለማና የብርሃን፤ የመሆንና ያለመሆን አዛዥ ጊዜ ብቻ ነው፡፡" አለች በሆዷ፡፡

"እና መቼ ነው የሚመለሰው አልሽኝ?" አጠያቃቸውን ለማሳመር እንጂ መቼ እንደሚመለሱ እንዳልነገረቻቸው ያስታውሳሉ፡፡ መልሷን ሳይጠብቁ ሌላ ጥያቄ አስከተሉ፡፡ "እኔምልሽ እህተ ጊዎርጊስ ባለፈው ክፉ ክፉ ወሬ ያሶራብሽ ሰው ነገር እንዴት ሆነ?"

"ኧይ አባ የሰው ስኬት የሚቆረቁረው ስንት አይነት ሰው አለ መሰለዎት፡፡"

"እምምምም. . . ልክ ነሽ ልጄ፡፡ በየ ቤቱ ስንት የይሁዳና የአሪዎስ ጭፍሮች አሉ፡፡" ሲሏት ፈለጉት ገብቷታል፡፡ እንኳን ይቺንና . . .

"ልክ ነዎት አባ ስንት የሰው ኑሮ የሚያማስል ሞልቷል፡፡" አፀፋውን መለሰች፡፡ መምሬ ጣሰው ከዚህ በላይ ባሽሙር መቀጠል አልፈለጉም፡፡ ነገሩ ሁሉ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ሆነባቸው፡፡ ከዚህ የባሰ ድብብቆሽ ውስጥ መግባት ተገቢ እንዳልሆነ አስበው ግደይ የነገራቸውን በሙሉ ሊያፈርጡት ወሰኑ፡፡ ወትሮውንስ ቢሆን ጊዜና ቦታ አልመቻች ብሏቸው እንጂ ግደይ ሚስጥረኛ መስሎ ካጠገቧ እንዳይጠፋ ያደረጉት ለዚህ አይደል፡፡

"እስቲ በሩን ዘግተሸው ነይ ልጅ ኤልሳ" አሏት ወደ ኋላ ተስተካክለው እየተቀመጡ፡፡ ከመቀመጫዋ ከተነሳች በኋላ ነበር ንግግራቸውን ያስተዋለችው መምሬ ጣሰውን ካወቀቻቸው ጀምሮ አንድም ቀን ኤልሳ ብለው ጠርተዋት አያውቁም፡፡ "አምልጧቸው ነው ወይስ አስበውበት?" ሳቋ መጣ፡፡

አባም ፊልም እንደሚያሰሯት ዳይሬክተሮች. . . ያያቷ ቤት ውስጥ አለከመኖር ተገን አርገው. . . ልታሽማቅቃቸው ስላልፈለገች በሩን ዘግታ ተመለሰች፡፡

**ይቀጥላል!**

# የጣና ዳር ለቅሶ

ምናለ ሉ

ቀኑ መሽቷል፤ ፀሐይ ብርሃኗን ለመፈጸም ታዘጋግማለች። ሞቅ ብላ የዋለችው ባሕር ዳር ቀዝቀዝ ብላለች፤ ከወደ ሰሜን የሚነፍሰው ነፋስ እርጥበትን አዝሏል! ሰራተኛዉ ከየመስሪያቤቱ ወጥቷል፤ ተማሪው ከየትምህርት ቤቱ ተበትኗል፤ ከተሜዎቹ በስራም ይሁን በሌላ ጉዳይ ተወጥሮ የዋለውን አእምሮአቸውን ለማፍታታት በቡድን ወይም በተናጠል ሆነው ወደ መዝናኛ ቦታዎች ጎራ ብለዋል። ጣናን ሳይጎበኝ እና ሳይሳለም ውሎ የሚያድር ማንም የለም። ግማሹ ጨርቅ ያጥባል፤ከፊሉ ይዋኛል፤ ከፊሉ ደግሞ በየዳርቻው ተቀምጦ ግርማ ሞገሱን ያደንቃል። ጣና ዛሬም እንደተለመደው ያንን የሚማርክና ህይወት የሆነውን ነፋሻማ አየር ለተጋባዞቹ ለግሷል፤ ከማንጎ መናፈሻ እስከ ጣና ሐይቅ ሆቴል መዳረሻ የዳርቻው መንገድ በአዝግም ተጓዦች ተጨናንቋል፤ ግማሹ ወደ ሰሜን ግማሹ ወደ ደቡብ ይተማል፤ በተለይ ጥንዶች ሰፈውን ስፍራ ሸፍነውታል። የጣናን ተፈጥሮአዊ ማንነት ዘወትር የማያደንቅ በውሃው የማይንቦጫረቅ አንድም የከተማዋ ነዋሪ የለም።

ገበየሁ ከሚያፈቅራት ሴት ጓደኛው ጋር ወደ ጣና አቅንቷል።

“ህሊና ዛሬስ ፍዝዝ ብለሻል ምነው?! ደግሞም የተጨናነቅሽ ትመስያለሽ ምክንያቱ ምንድን ነው?” አለ ገበየሁ ጉያው ውስጥ የወሸቃትን ህሊናን ፊቷን ከወደ ጎን እየተመለከተ።

“ኧህ … እኔ እንጃ !” አለች ህሊና በረዥሙ እየተነፈሰች።

“ እንዴት?” አለ ገበየሁ።

“ምን እንደሆነ ማወቅ አልቻልኩም ብቻ ግን ጭንቅ ጭንቅ ይለኛል” አለች ህሊና ፊቷ ላይ የሚዘናፈለውን ውስን ውብ ጸጉሯን ወደ ኋላዋ እየመለሰች።

“እንደ እኔ ራት ብትሰቅይ ኑሮ አትጨናነቂም ነበር። ምናልባት የሆድሽ ነገር ጭንቅ ስለሆነ ካፌው የሚዘጋ መስሎሽ ይሆናል” አለ ገበየሁ ቀልድ ቢጤ ጣል በማድረግ ህሊናን ከገጠማት ድንገተኛ ጭንቀት ለመገላገል።

“ውጤት አትሰቅልም እንጂ ካፌ በመስቀልህስ ‘ቀዳሚ ርዕሰ ሳዕላይ ካፌ ሰቃይ አቤ ገበየሁ’ ያሉህ ጓደኞችህ ወደው አይደለም … እንዳንተ መሰለኩህ ” አለች ህሊና ፈገግ ብላ።

“እርሱስ ልክ ነሽ በእንቅልፋሞች እና በካፌ ሰቃዮች ላይ ቫት( የታክስ ቀረጥ) ቢጣል አንቺ እና እኔ ምን ይውጠን ነበር?”

“ ኧረ ባክህ እኔ…! እንቅልፋም ነሽ እያልከኝ እኮ ነው!”

“እናስ እንኳን ሌሊት እና እኩለ ቀን አሁን ልታንቀላፊ ዳርዳር እያልሽ አይደል! አሁንስ ፈራሁት ወደዚህ ሐይቅ እንዳትጠልቂ እንጂ … ለማንኛውም እኔ በዚህ በኩል ልሁን እንቅልፍ እኮ የማያደርገው የለም” አለና ከነበረበት በተቃራኒ ከእርሷ በስተግራ በጣናና በእርሷ መካከል ሆነ።

“እንቅልፍ እኔ ዘንድ አይቃጣኝም ”

“አይ ባይቃጣሽ ሳይጠቅስሽ አይቀርም አናንተን ችኮችን የማይጠቅስ ማን አለ?” ተሳሳቁ።

ከፖሊ በር አንስተው በሙንላይት በኩል አድርገው በጣና ዳር ወደ ጣና ሆቴል “ወካቸውን» ቀጥለዋል።

ሁለቱም የ3ኛ ዓመት የኢንጅኔሪንግ ተማሪዎች ናቸው። ገበየሁ የሲቪል ምህንድስና ተማሪ ሲሆን ጠየም ያለ ጸጉረ ከርዳዳ ቁመተ ሸበላ ነው፤ ህሊና እጅግ የተዋበች፣ የደም ግባቷ ያማረ፣ ቆንጆዎች የማይተካከሏት እና እጥር ምጥን ያለች መልከ መልካም ናት፤ እንደ ልብስ መስቀያ ተነቅሶ የተቆላመመው ፀጉሯና እንደ በረዶ የነፁት ጥርሶቿ ልዩ ውበት ነበራቸው።

“አይ ዋተሮች ምነው ውትር በላችሁ ብትቀሩ እስኪ ህሊና ይህን የመሰለ የሀገራችን ሃብት በቆሻሻ ተሞልቶ ንፅህናውን ብታስጠብቁለት?”

ህሊና ፈገግ ለማለት ስትሞክር “እውነቴን ነው ቀልድ አይደለም!” አለ ገበየሁ ኮስተር ብሎ።

በቀልድ ፈክቶ የነበረው ፊቱ በቅጽበት ተለወጠ፤ የእሳት ነበልባል የገረፈው እርጥብ ቅጠል መሰለ።

“ጣና እኮ ፈጣሪ በደግነቱ የቸረን ብርቅ እና ድንቅ ሃብታችን ነው።”

ርግጥ ነው ጣናን ማየት፣ማስተዋል እና መመልከት መሃል ባህሩን እና ማዶ - ማዶውን ካልሆነ ዳርና ዳሩን ማየት በጉረቤት ክብርን ያስነሳል፤ ልክስክሶች ያሰኛል፤ የባለቤትን አንገት ያስደፋል። የሳሙና እና የሲጃራ መጠቅለያዎች ባዶ ሃይላንዶች እና ሌሎች የማይበሰብሱ ቁሶች በተፈጥሮ ጉድለት ሳይሆን በሰው ልጅ ጉድለት ለጣና የተቸሩት ያመረቀዙ የመቀመጫ ቁስል እና ያልተጠፈሩ የእግር ሸለፈቶች ሆነውታል።

“ህሊና እስኪ ተመልከች ይህን የፌስታል እና የሃይላንድ መዓት!”

“አንተ ደግሞ በማያስጨንቀው መጨነቅ ልማድህ ነው።” አለች ህሊና ።

“ስታናድጅ…! የጣና እንዲህ መበከል ያላስጨነቀኝ ሌላ ከዚህ የበለጠ ምን የሚያስጨንቀኝ ነገር አለና ነው አንቺ! ጣና ቢኖር አይደል እንዲህ የምንዝናናው!” አለ ገበየሁ። ሰውነቱን የንዴት ግለት እያንገበገበው።

ጣና ሆቴል መዳረሻ ለመድረስ እንደተቃረቡ ከጉዞአቸው በስተግራ በኩል ሁለት ወጣቶች ዋርካው ስር ተቀምጠው፤ ጸጉራቸው ተንጨፍሮ፤ ጉንጫቸው ጥጥ የታመቀ ጆንያ መስሎ፤ አጠገባቸው ጫት የያዘ ፌስታል ተቀምጦ፤ የተወሰኑ ፌስታሎች ባህሩ ላይ ተንሳፈው አዩ። ገበየሁ ይበልጥ ተበሳጭቶ፣

“ትንሽ አይሰቀጥጣችሁም ይህንን የፌስታል መዓት እያመጣችሁ ውሃው ውስጥ ስትጥሉት” አለ።

ሁለቱም ከተቀመጡበት ቀና ቀና ብለው ወደነ ገበየሁ አይናቸውን አፍጥጠው ተመለከቷቸው።

አንደኛው ከቅጽበት ተነሰቶ ወደ ገበዬሁ እየተምዝገዘገ “ምናባህ ትጮሃለህ አንተ” አለና ወገቡን ጠምዝዞ ወደ ጣና አሽከረከረው። ገበየሁ ወደ ባህሩ ላለመግባት ሲታገል ሌላኛው እየተንደረደረ ሂዶ ወደ ባህሩ ገፈተረው ገበየሁ ድንቡቅ አለ … በዚያው ስምጥ … አለ ።

ህሊና በድንጋጤ ተውጣ የጨው ሀውልት ሆነች፤

“ወይ ‘ድሌ! ወይ’ድሌ! ገበኧ··ኧየሁ…” አለች ባህሩ ዳር አየተንቦራቸች። ሁለቱ ጎረምሶች የመጣው ይምጣ ብለው ጥለዋት ሄዱ።

“ወይኔ … ወይኔ ወዮ! ኧሀሀሀ ኧሀሀ… ” ተንበርክካ ተንሰቀሰቀች። መሬቱን የሚያስሱት እጆቿ ከንጣፍ የሲሚንቶ ድንጋይ ውጭ የሚጨብጡት አልነበራቸውም።

“ብቻየን… ገበኧ··.የሁ!”። የሚሰማት የለም። ምሽት መጥቷል። ድንግዝግዝ ብሏል።

“ዉ… ዋይ ዉ……ዋይ” ትጮሃለች ሰሚ የለም። ዋርካዉ ላይ ያሉት አእዋፍ አብረው ይጫጫሃሉ።

“ጣና ተቆርቋሪህን አትብላ ገበየሁን ትፋ… ” እያሉ ሙሾ ይጠራሉ ።

አላቃሽ የሌላቸው ለቀስተኞች …

ꩨꩨꩨꩨꩨ

# የግጥም ጥግ

ውዴ

ልቤን በምድረ በዳ፣
ትተሽኝ እንዳልጎዳ፣
ዘልቀሽ አጠጭኝ ከፍቅሽ፣
እንድኖር በልብሽ፣
የኔ አሳቢ የመውደድ ልክ፣
የፍቅር የራሱ መልክ፣
የጥም ቆራጭ የዘላለም፣
እንዳንች አይነት ከቶ የለም።

ꩨꩨꩨꩨꩨ

ባጣ ብነጣ ምን ተዳዬ፣
ሕልሜ ቀድሞኝ ከኋላዬ፣
ይሁን ብሎ ከፃፈልኝ፣
መጠበቅ ነው የኔ እስኪገኝ።
ባይሆን…
እስክነቃ ከእንቅልፌ፣
ይህንን ሁሉ አልፌ፣
የቀደመኝ ህልሜም ይምጣ፣
ይፈታልኝ ያለኝ ጣጣ።

ከሠለሞን ሙሉ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የዌብሳይት ማኔጀር

## ውድ የናይል ጋዜጣ ተሳታፊዎችና አንባቢያን

*ለዘወትር ትብብራችሁ እያመሰገንን በጋዜጣችን ላይ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512 ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል አድራሻችን gracetsegi@gmail.com በመላክ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን።*

ዝግጅት ክፍሉ

# Do Students' Diets Meet Nutritional Requirements based on the Standard Dietary Recommended Guidelines?

## Bahir Dar University in Focus

Girma Kibatu, PhD
girmakibatuberihie@gmail.com
Biological Inorganic Chemistry

Malnutrition, which is caused by protein-energy malnutrition and micronutrient deficiencies, has continued to be a major public health problem in Ethiopia. The term malnutrition is a broad term that includes both under-nutrition and over-nutrition, but in this paper, I use specifically the former in an attempt to examine the nutritional requirements of diets at BDU.

Indeed, malnutrition is often used specifically to refer to under-nutrition for a condition that results from eating a diet in which nutrients are frequently deficient in macronutrients (protein, carbohydrates and fat, leading to protein–energy malnutrition), micronutrients (electrolytes, minerals and vitamins, leading to specific micronutrient deficiencies) or both.

Besides illness, infections and deaths in affected communities, non-communicable nutrient-related diseases are one of the major risk factors for poor performance in schools and jobs in developing countries. Over-nutrition is not given priority here at least for now.

Some of the common macro and micronutrient deficiencies diseases associated with undernutrition in developing countries include Osteomalacia (calcium), Anaemia (Iron and or Vitamin B12), Vitamin B deficiencies ( B2, B6), stunting (Zinc), Nueral Defects (B9 folic acid, copper), Goitre and thyroid disorders (iodine, selenium), Scurvy (vitamin C) and Xerophthalmia (Vitamin A).

Poverty along with its determinants is the main underlying cause of malnutrition. Insufficient supply of essential macronutrients and micronutrients and severe or frequent infections and diarrhoea at any stage in the cycle of human development (infants, children, adolescents, or adults) are the direct causes of malnutrition. The high prevalence of bacterial and parasitic diseases in developing countries also contributes greatly to malnutrition. Similarly, malnutrition increases one's susceptibility to and severity of infections, and is thus a major agent of illness and death.

***Food functionality refers to a balanced diet, which consists of the proper quantities and proportions of foods/ nutrients that are needed to maintain health, growth and productivity.***

Access to safe food, adequate and stable food availability and bio-utilization has always been mankind's first concern on food security. Food functionality and food safety are also the basic conditions for food quality. Food functionality refers to a balanced diet, which consists of the proper quantities and proportions of foods/nutrients that are needed to maintain health, growth and productivity. Nutrients known to be essential for human beings are proteins, carbohydrates, fats, fibres, minerals, vitamins and water. On the other hand, food safety implies the practices to maintain the quality of food within acceptable limits, and prevent food pollution from chemical and microbiological contaminants that may create risks for human health. Overall, when combined with regular exercises, eating a balanced and healthy diet provide the body with basic human nutrition.

Different body types require different amount and type of nutrients. This can depend on age, gender, illness and the rate at which your body works. Ethiopian University students (mean age 17) are middle adolescents. It is clear that we need to invest in these unique generations as they are crucial in building a better future of the country. Nutrition influences growth and development in all stages of life. However, adolescents require the greatest due intense physical, psycho-social and cognitive development. Moreover, there is evidence that unfavourable nutritional profile during adolescence is related to adverse health outcomes in later adult life.
It is; therefore, important that the food and drink served for the students should nutritionally functional and safe for eating. Similarly, in order to function well, the human body must have adequate calories and nutrients. In addition, foods that are consumed must be sanitary and palatable.

To begin with, the awareness of what and how much food a student consumes is crucial in achieving and maintaining a healthy body. Foods available in the university canteens show a great deal of variation in terms of ingredients and manner of preparation. It is; therefore, necessary to evaluate nutritional and micronutrient status, dietary environments, current dietary intakes and behaviours of Bahir dar university students compared to the Recommend Dietary Guidelines. Furthermore, it is important to collect ideas and suggest evidence based recommendations and possible strategies in order to facilitate the development of effective and tailored intervention programs that aim to improve the quality and condition of food and healthy eating behaviours of university students.

Bahir Dar University students' 7-day meal plan generally focuses on grains and beans almost every day and a few cow meat – which may or may not satisfy their short term calorific need based on a 2,000-calorie diet (see Table 1).

The meal plan for all students in Bahir Dar University obtained from student services office is outlined in Table 1 (left).

**Table 1. Meal Plan for Bahir Dar University students' Cafeterias'**

| Days/ Time | Monday | Tuesday | Wednes-day | Thursday | Friday | Satur-day | Sunday |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Break fast | Injera Fir fir Bread Tea | Sauce Bread Tea | Bread Tea | Rice Bread Tea | Injera Fir fir Bread Tea | Sauce Bread Tea | Rice Bread Tea |
| Lunch | Shiro ½ Injera Pasta Bread | lentils stew Injera | lentils stew Injera | Lentils stew Injera | Shiro ½ Injera Pasta Bread | Shiro ½ Injera Pasta Bread | Lentils stew Injera |
| Dinner | Bean Kik Injera | Bean Kik Injera | Bean Kik Injera | Meat therefore Stew Injera | Bean Kik Injera | Bean Kik Injera | Meat therefore Stew Injera |

continued on page 13

# እንግዳችን

## “ምርምር ሲባል ዝም ብሎ መመራመር እና የምርምር ውጤቱ በኢንተርናሽናል ጆርናሎች ላይ የሚታተም ካልሆነ ዩኒቨርሲቲው ራዕዩን ለማሳካት አይችልም::”

ዶ/ር እንየው አድጐ

**የዚህ ወር እንግዳችን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ሲሆኑ የህይወትና የሥራ ተሞክሯቸውን ከናይል ጋዜጣ ዘጋቢ ሙሉጐጃም አንዱዓለም ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!**

ናይል፡- በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እያመሰገን ሙሉ ስምዎትንና የሥራ ኃላፊነትዎን ቢያስተዋውቁን?

ዶ/ር እንየው፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡ ስሜ እንየው አድጐ ይባላል፡፡ በግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ት/ክፍል መምህር ነኝ፡፡ ለጊዜው የኃላፊነት ሥራ የለኝም ፕሮጀክቶችን እያስተባበርኩ እገኛለሁ፡፡

ናይል፡- የትውልድ ቦታዎንና የአስተዳደግ ሁኔታዎን ቢገልፁልን?

ዶ/ር እንየው፡- እኔ የተወለድኩት በምዕራብ ጐጃም ዞን ደቡብ አቸፈር ወረዳ ልዩ ስሙ «ጐታአቦ» ከተባለ ቀበሌ ሲሆን ከገበሬ ቤተሰብ ነው ተወልጄ ያደኩት፡፡ በዚያን ጊዜ ማህበረሰቡ ለትምህርት ያለው አመለካከት የወረደ ስለነበር አብዛኛው ሰው ትምህርት አይማርም ነበር፤ ነገር ግን የእኔ አባት ከአካባቢው ማህበረሰብ የተሻለ አመለካከት ስለነበረው ምንም እንኳ የኔ ታላላቆች በቁጥር ስድስት ያህሉ ሳይማሩ እኔ ከቤቱ ሰባተኛ ልጅ ሆኘ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ተልኬ ከአንደኛ ክፍል እስከ 8ኛ ክፍል ዱር ቤቴ እየተመላለስኩ ተምሬ የስምንተኛ ክፍል ትምህርቴን እንዳጠናቀቅኩ ወደ ዳንግላ ሄጄ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ተምሬ እንደጨረስኩ ወደ ኮሌጅ ገብቻለሁ፡፡

ናይል፡- ስለ ቤተሰብዎ ቢያጫውቱን?

ዶ/ር እንየው፡- እኔ ባለትዳርና የ3 ልጆች አባት ስሆን ጀርመን ሀገር ለትምህርት ሄጄ ለ12 ዓመታት ያህል ስለቆየሁና ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ የዛሬ አስራ አምስት ዓመት አካባቢ ትዳር መስርቼ የሁለት ሴት ልጆችና የአንድ ወንድ ልጅ አባት ሆናለሁ፡፡

ናይል፡- በህይወትዎ የሚወዱት ነገር ምንድን ነው? የሚጠሉትስ?

ዶ/ር እንየው፡- በህይወቴ የምወደው ነገር መሥራት በጣም ያስደስተኛል፤ የምጠላው ደግሞ አለመሥራትን ነው፤ አንድ ቀን አልፎ ወደ ማታ አካባቢ ሆኖ ሳየው ብዙ ሥራ በመሥራት ያሳለፍኩት ቀን ከሆነ ውስጤ በደስታ ይሞላል፡፡ ነገር ግን ያለምንም ሥራ ያሳለፍኩት ቀን ከሆነ ቀኑን ያለሥራ ማሳለፌ ብቻ ሣይሆን ደስታዬንም ይነጥቀኛል፡፡ ስለዚህ እኔ የምወደውና የምጠላው ነገር የሚያተኩረው በመሥራትና ባለመሥራት መካከል ነው፡ ፡

ናይል፡- የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪዎን የትና በምን የትምህርት መስክ ሰሩ?

ዶ/ር እንየው፡- እኔ የመጀመሪያ ዲግሪ የለኝም፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪ የሌለው ሰው እንዴት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሊኖር ይችላል ብለሽ ልትገረሚ ትችያለሽ፡፡ ከዳንግላ አስራ ሁለተኛ ክፍልን እንደጨረስኩ ደብረዘይት የእርሻ ኮሌጅ ገብቼ የዲፕሎማ ትምህርት ተምሬ እንደጨረስኩ በባሌ ክፍለ ሀገር የቡናና የሻይ ልማት የልማት ሠራተኛ ሆኜ ሁለት ዓመት ከ10 ወር አካባቢ አገልግያለሁ፡ ፡ በኮሌጅ ውስጥ በነበረኝ ጥሩ ነጥብ ተወዳድሬ ጀርመን አገር ባወጣው «ስኮላርሽፕ» ስላለፍኩ በዚያን ጊዜ ምስራቅ ጀርመን ከተባለው አገር ከሄድኩ በኋላ ያላቸውን ካሪኩለም 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ወይም ዲፕሎማ ያለው በቀጥታ ገብቶ የማስተር ትምህርቱን ለማጠናቀቅ አምስት ዓመት የሚወስድ ነበር፡፡

ስለሆነም የዲግሪውን ትምህርት ለማጣጣም 3ኛ ዓመት ላይ በ ”Assignment” መልኩ እየተሰጠን ሰርተን ሁለት ዓመት ደግሞ “ቲስስ” በመሥራት የአምስት ዓመት የማስተር ትምህርቴን እንደጨረስኩ ወደ ኢትዮጵያ ሳልመለስ እዚያው የዶክትሬት ዲግሪ የትምህርት እድል ስላገኘሁ በቀጥታ ተምሬ አጠናቀቅኩ፡፡ ጀርመን አገር 5 ዓመት ለማስተር ትምህርት 1 ዓመት የአገሩን ቋንቋ ለመማር፣ 3 ዓመት የ”PhD” ትምህርትና ሶስት ዓመት ደግሞ በሥራ ላይ በአጠቃላይ 12 ዓመት ቆይቼ ተመልሻለሁ፡፡

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መቼ ሥራ ጀመሩ? በዩኒቨርሲቲው አመራር ቦታዎች ላይ አገልግለዋል? በምን በምን የሥራ ዘርፎች ላይ ሠርተዋል? ያጋጠመዎት ተግዳሮቶችስ?




ዶ/ር እንየው፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሥራ የጀመርኩት እ.ኤ.አ. በ2008 ዓ.ም ጥር ላይ ነው፡፡ ከዚያ በፊት አማራ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ምርምር ዳይሬክተር ሆኜ በማገልገል ላይ እያለሁ የአሁኑ ግብርናና አካባቢ ሣይንስ ኮሌጅ የቀድሞው ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ፋኩልቲ ሲቋቋም የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ት/ክፍል ካሪኩለም ዝግጅት ላይ በዋናነት ሠርቻ ስለነበር

ዶ/ር ፀሐይ ጀንበሩ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሆኖ እየሰራ እያለ የካሪኩለሙን ዝግጅት ይመራው ስለነበር በተወሰነ መልኩ ተገናኝተን ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ የፋኩልቲው ዲን ሆኖ የሚሰራው ነፋሱን በሰሣይ ይማረውና አሁን በህይወት የሌለ ዶ/ር ፅጌ ገነት በስልክ ደውሎ ፕሬዚዳንቱ ወደ ዩኒቨርሲቲው እንድትገባ ይፈልጋል ብሎ ነረረኝና እኔም እስቲ ትንሽ ላስብበት ብዬ ከቆየሁ በኋላ የምርምር ዳይሬክተር ሆኘ 5 ዓመት ስላገለገልኩና በኢንስቲትዩቱ ውስጥም እኔን የሚተኩ የዶክትሬት ትምህርት ያጠናቀቁ ስለነበሩ ሥራውን ለተተኪዎች አስረክቤ ጥያቄውን በመቀበል ወደ ዩኒቨርሲቲው ተቀላቀልኩ፡፡ ከገባሁ በኋላ በተለያዩ የአወራር ቦታዎች አገልግያለሁ፤ ለመጥቀስ ብሞክር እንደገባሁ የፋኩልቲው የድህረ ምረቃ ዲን በመሆን ከዚያም በዚያን ጊዜ እንዳሁኑ በምክትል ፕሬዚዳንትነት ስላልተዋቀረ የዩኒቨርሲቲው የምርምር ኃላፊ (officer) ሆኘ ካገለገልኩ በኋላ ፋኩልቲው ወደ ኮሌጅ ራሱን አሳድጐ በምክትል ዲንነትና በዋና ዲንነት በተከታታይ ሠርቼ ጃፓን አገር «የቪዚቲንግ ሣይንቲስት» ቦታ አግኝቼ ስሄድ ኃላፊነቱን ለሌሎች አስረክቤ ሄጄ ያሄድኩ ብትንተናው አጠናቅቄ ተመልሻለሁ፡፡ በኃላፊነት ቦታ ሥሰራ በርካታ ተግዳሮቶች ገጥመውኛል፤ በኃላፊነት ቦታ መሥራት ከብዙ ሰው ጋር ያገናኛል፤ የብዙ ሰዎችን ባህሪ ማስተናገድ ከባድ ነው እንዲሁም ሥራ መስራትና ባለጉዳይ ማስተናገድ የማይጣጣሙ ስለሆነ ሁለቱን አጣጥሞ ለማስኬድ ከባድ ነው፡፡ ካጋጠሙኝ ተግዳሮቶች ውስጥ ዋናውና ፈታኙ ዩኒቨርሲቲው የBPR ሥራ ሲያዋቅር ዲፓርትመንቶች ስላፈረሱ ሁሉም የተማሪ ጉዳዩ በቀጥታ ወደ ዲን እየመጣ ሁሉንም ዲኑ ይፈታዋል ተብሎ ስለነበር የዚያን ሁሉ ችግር ለመፍታት አስቸጋሪ በመሆኑ እኔ በበኩሌ እንደ ዲንነት የዲፓርትመንቶችን መፍረስ አልተቀበልኩትም ነበርና ከተለያዩ የበላይ አካላት ጋር

⇨

# እንግዳችን ...

እየተነጋገርኩ መፍትሄ ሳላገኝ አጠቃላይ በኮሌጁ ውስጥ የሚነሱ ቅሬታዎችን ሁሉ እንዳይ የተገደድኩበት ወቅት ነበር።

ናይል፡- በ2007 ዓ.ም ባበረከቷቸው የምርምር ውጤቶች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ምርጥ ተመራማሪ ሆነው በመመረጥዎ በናይል ጋዜጣ ስም እንኳን ደስ አለዎ እያልን ስለምርምሮቹዎ ትንሽ ቢያጫውቱን? የምርምር ውጤቶቹስ የትኩረት አቅጣጫ በምን ዙሪያ ነው? ምርምርንና ፕሮደክትን እንዴት ይገልፁታል?

ዶ/ር እንየው፡- የማሳተም ሥራ ከዓመት ዓመት እንደሚለያይ የታወቀ በመሆኑ አጋጣሚ ሆኖ በ2007 ዓ.ም በርካታ የምርምር ፅሁፎችን ያሳተምን ሲሆን እኔ በቻ ሳልሆን ሌሎችም በዩኒቨርሲቲው እውቅና ያገኘንበት በመሆኑ እኔም ደስ ብሎኛል። ስለምርምር ብናወሳ የምርምር ሥራዎች መሠረታቸው ከፕሮጀክት ጋር ይያያዛል። የእኔም የምርምር ፕሮጀክት «ዋሴ ጣና» የተባለው የውሃ ፍሰትንና የአፈር ክለትን በጣና ተፋሰስ ላይ የሚያጠና ምርምር ስለሆነ የዶክትሬትና የማስተር ተማሪዎች ይሳተፋሉ። ተማሪዎቹ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብቻ ሳይሆኑ ከውጭ አገርም በተለይ ከጌንትና ከኖቨል ዩኒቨርሲቲ የሚመጡ ተማሪዎችን ያሳትፋል። ምርምሩ በተለይ ጣና ሀይቅ ላይ የሚገቡ ደላሎች ዙሪያ ላይ የተሰሩ በርካታ ፅሁፎችን የያዘ ነው። የትኩረት አቅጣጫዎችም እኔ የአፈር ባለሙያ እንደመሆኔ መጠን በሀገራችን ጉልቶ የሚታየው ችግር አፈር በዝናብ ታጥቦ የመሬት መራቆት በስፋት መከሰት ስለሆነ የአፈር ንጥረ ነገር ክለትን ለመከላከል ጣና ሀይቅ በምን ያህል ፍጥነት በደለል እንደሚሞላና ገባር ወንዞችም ወደ ሀይቁ ይዘውት የሚገቡትን የደለል መጠን ለማወቅ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው። እኔ የማስተባብራቸው ፕሮጀክቶች ብቻዬን ሣይሆን ከሌሎች አገሮች ከተውጣጡ ታዋቂ ፕሬፌሰሮች ጋር በመተባበር ነው።

ፕሮጀክቶች ለዩኒቨርሲቲው ያላቸውን ፋይዳ ለመዘርዘር ስሞክር በዋናነት የሰው ኃይል አቅም መገንባት ነው፤ ከዚያም ባሻገር የቁሳዊ አቅሙን ለማጠናከር ጉልህ አስተዋፅኦ አላቸው። ምክንያቱም ምናልባት በዩኒቨርሲቲው አቅም መገዛት የማይቻሉ በጣም ውድና ዘመናዊ የሆኑ ለቤተ-ሙከራ ሥራ የሚያገለግሉ አቃዎችና ተሽከርካሪዎች በፕሮጀክቱ አማካኝነት ተገዝተዋል፡ ፡ እንዲሁም ለተለያዩ ሰዎች የሥራ እድል ተፈጥሯል፤ እኔ በማስተባብራቸው ሁለት ፕሮጀክቶች ብቻ እንኳ ከ45-50 የሚደርሱ አርሶ አደሮችን በተለያየ ቦታ ዳታ እንዲሰበስቡ ተቀጥረው በየወሩ ደመወዝ እየተከፈላቸው ለረጅም ዓመታት የቆዩና እንደ ሥራቸው ውጤታማነት ታይቶ በቋሚነት የተቀጠሩም አሉ። ስለዚህ የፕሮጀክት ምርምሩ ለዩኒቨርሲቲው በርካታ የዶክትሬት ማዕረግ ያላቸውን ሰዎች ከማበርከቱ በተጨማሪ የተለያዩ አኩሪ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 በአፍሪካ ውስጥ ካሉ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ጐራ ለመሰለፍ ራዕይ ሰንቆ እየሰራ ነው፤ ይህን ራዕይ ለማሳካት ምን መደረግ አለበት ይላሉ? ከአመራሩ፣ ከመምህራኑና ከአስተዳደር ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ቢገልፁልን?

ዶ/ር እንየው፡- እርግጥ ነው ዩኒቨርሲቲው ከአፍሪካ ውስጥ ግንባር ቀደም ለመሆን ራዕይ አስቀመጦ እየተንቀሳቀሰ ነው፤ ስለዚህ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን በምርምር ታዋቂ መሆን ይጠበቅበታል፤ ታዋቂ ለመሆን ደግሞ የምርምር ግባቶችን ማሟላት፣ የሚመራመሩ መምህራንን ማበቃት፣ የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ሙህራንን ማበረታታት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ወደ ሁለት ሺ አካባቢ መምህራን እንዳሉ እገምታለሁ፤ እነዚህን ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አብዛኛውን ቁጥር የሚይዘውን ወደ ምርምሩ እንዲገባ ማድረግ ይገባል። ምርምር ሲባል ዝም ብሎ መመራመር እና የምርምር ውጤቱ በኢንተርናሽናል ጆርናሎች ላይ የሚታተም ካለሆነ ዩኒቨርሲቲው ራዕዩን ለማሳካት አይችልም፤ ምክንያቱም ዩኒቨርሲቲው ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሆኗል አዚህ ደረጃ ደርሷል ሊባል የሚችለው በራሱ መምህራኖች ተሰርተው ከፍተኛ የምርምር ውጤት ባስመዘገቡት አቅሞች ልክ ተመዝኖ ደረጃው ስለሚታወቅ ነው፤ የሚታተሙት ፅሁፎችም ከፍተኛ የሚባሉ ሣይንሳዊ ጆርናሎች ላይ መሆን አለባቸው። ከአመራሩና ከሌሎች አካል የሚጠበቁ ነገሮች እንደኔ እምነት ለአንድ ዩኒቨርሲቲ መጀመሪያውም መጨረሻውም ሰው ነው፤ የሚል አቋም ስላለኝ ለሰዎች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንዲሁም ማበረታታትና ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ስለሆነ በውስጡ ያሉትን ማጣት ሣይሆን በውጭ ያሉትንም ታዋቂ ሙህራን የማምጣት ሁኔታ እንዲፈጠር አዳዲስ የአሰራር ስልቶችን መንደፍና ለምርምሩ ልዩ ትኩረት መስጠት ይገባል።

ናይል፡- ዩኒቨርሲቲውን ለምርምር ምቹ ለማድረግ ምን መሰራት አለበት ብለው ያምናሉ? እርስዎስ በበኩልዎ ምን አስተዋፅኦ አበርክተዋል?

ዶ/ር እንየው፡- አንድ ዩኒቨርሲቲ ብቁ የሆነ ቤተ ሙከራ ከሌለው "ከኃይስኩል" አይለይም፤ ስለዚህ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ቤተ-ሙከራዎች ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት መሥራት በርግጠኝነት ዩኒቨርሲቲውን የተሻለ የምርምር ተቋም ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ይህን ለማጠናከር ውጭ ካሉ ተቋማት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ማጠናከርና አብሮ የመስራት ሂደቱንም ማሻሻል ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ዩኒቨርሲቲው "እንደደሴት" እዚህ ቁጭ ብሎ በውስጡ ባሉት ሙህራኖች ብቻ የትም ሊደርስ አይችልም። ካደጉ አገሮች ጋር የጋራ ፕሮጀክቶችን በመፍጠር ችግር ፈች ምርምር ማካሄድ ይችል ዘንድ መምህራኑን ማብቃት ብቻ ሣይሆን ለምርምሩ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሁሉ ማሟላት፣ ፕሮፌሰሩ ከሌሎች ታዋቂ ፕሮፌሰሮች ጋር እንዲሰራ ወይም ዶክተሩ ከዶክተሩ ጋር የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር አዳዲስ የምርምር ስልት እንዲያውቅ መደረግ አለበት።

አዳዲስ ምርምሮችን ከሠራን ደግሞ ትልልቅና ታዋቂ ጆርናሎች ላይ የሚወጡ ፅሁፎችን መስራት ይቻላል፤ መምህራኑ በተመራመሩ ቁጥር ችግሩን ለመቅረፍ ብዙ ስራዎችን ስለሚያከናውን በሚያስተምርበት ወቅት ክፍል ውስጥ የሚሠጠው ትምህርት ከነባራዊ ችግሩ ጋር ተያያዥነት ይኖረዋል፤ ተማሪውም ይበልጥ ተጠቃሚ ሆኖ ስለሚወጣ የትምህት ጥራት ይረጋገጣል፤ ለተማሪው የሥራ ዕድል ይጨምራል። ስለዚህ ምርምሩ ለምርምር ብቻ ሣይሆን ተያያዥ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። በምርምር የተገኙ መልካም ውጤቶች ሁሉ ወደ ማህበረሰቡ ወስደን ችግር ፈች የማህበረሰብ አገልግሎት እናካሂዳለን ማለት ነው።

በበኩሌ ብዙ አስተዋጽዖ አድርጌያለሁ ብዬ ባልገምትም ከጃፓን አገር በተገኘው "ካካኒ" በተባለው ፕሮጀክት አማካኝነት ሦስት ሰዎች የዶክትሬት እድል አግኝተው አራተኛውም በዝግጅት ላይ ነው። ከቤልጅየም አገር በተገኘም ፕሮጀክት ቁጥራቸውን በውል ባታወቁም የሚማሩ ተማሪዎች አሉ። የዚህ ውጤት በሚቀጥሉት አስር አመታት በፕሮጀክት አማካኝነት የትምህርት እድል የሚያገኙ ከአርባ በላይ በዶክትሬት፣ ከ ስልሳ እስከ ሰባ የሚደርሱት ደግሞ በማስተርስ ተምረው በሀገራችን ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍና በተለይ ገና በመቋቋም ላይላሉ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች በቂ ምሁራን በማስገኘቱም ስራ ውስጥ የኔ ጥረት አለበት ብዬ አምናለሁ፤ ለወደፊቱም መሰረታዊ የትምህርና የምርምር ቁሳቁሶችን ማሟላት እንደሚቻል አምናለሁ።

ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባሳለፏቸው የሥራ ዘመናት ስኬታማ ነኝ ብለው ያምናሉ? እንዴት?

ዶ/ር እንየው፡- እኔ ስኬታማ ነኝ ብዬ አፌን ሞልቼ መናገር ይከብደኛል፤ በርግጥ ከላይ በገለጽኳቸው ነገሮች ላይ የተወሰነ ድርሻ ቢኖረኝም የኔን ስኬታማነት የሚያጎላው ከሌሎች ጋር በቅንጅት የተሠሩ ሥራዎች ውጤት ሲሆን ስኬታማነቴን ሌሎች እንዲገልጹት ልተወው ትንሽም ብትሆን አስተዋጽኦ ለማድረግ ሞክሬአለሁ፡ ፡

ናይል፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለዎት?

ዶ/ር እንየው፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የምፈልገው ዩኒቨርሲቲው በኔ ግምት አሁን ካለበት በላይ ማደግ መመንደግ የሚችል ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ ነው። ይህንን እንድል የሚያስደፍረኝ ከአካባቢው የወጡ በርካታ ሙህራን በአገር ውስትም በውጭም ከታዋቂ ሳንቲስቶችን ጋር የካበተ ልምድ ያላቸው ስላሉና የተመሠረተው በክልሉ ከተማ ስለሆነ ለመኖር ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ አምናለሁ፤ ለመስራትም ምቹ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚደርስ ሙሉ እምነቴ ነው። ነገር ግን በርካታ መሟላት የሚገባቸው ነገሮች አሉ፤ ለአብነት ያህል ብጠቅስ ለእኔ ለአንድ ዩኒቨርሲቲ ቤተ- መፅሐፍትንና ቤተ ሙከራዎችን በስርዓት ማለትም በዘመናዊ መልኩ ማደራጀት መሠረታዊና ቁልፍ ተግባር ነው ብዬ አምናለሁ፤ ይሁን እንጅ ምን ያህል ቤተ- ሙከራዎች አሉን? ቤተ- መጽሐፍቶች ምን ያህል በዘመናዊ መልኩ ተደራጅተዋል? በውስጡስ ምን ያህል ዘመናዊ መጽሔቶችና ሌሎች ለምርምር የሚያግዙ መርጃ መሣሪያዎች ይገኛሉ? ስንል ጥያቄው ለሁላችንም ግልጽ ነው፤ ብዙ መሟላት የሚጠበቅባቸው ነገሮች ስላሉ እነዚህና ሌሎች ተዛማጅ ችግሮች ተፈተው መሟላት ያለባቸው እንዲሟሉ አመራሩ ካገዘ፣ አልታየም አተፋም የራሱን አስተዋጽኦ ካበተከተ ዩኒቨርሲቲው ትልቅ የማይሆንበት መንገድ አይታየኝም። ሁላችንም በቆይታችን ጊዜ ለተቋሙ አበርክተን ማለፍ ያለብን ነገር እንዳለ እምነት ጥለን ምናልባት በቅርብ ጊዜ ትልቅ ይሆናል የሚል የራሴ እምነት አለኝ፣ ለዚያም ደግሞ የምችለውን እስከምችል ድረስ አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው የምፈልገው።

ናይል፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም በጣም አመሰግናለሁ።

ዶ/ር እንው፡- እኔም አመሰግናለሁ።

# Man Shall Not Live by Bread Alone

By: Merhatsidk Mekonnen Abayneh

This year's 'public lecture' organized by Bahir Dar University on the eve of the fifth Tana High-Level Forum on Security in Africa had Ms. Louise Mushikiwabo as a special guest of honor to dwell on the contentious subject of 'Developmental State' in Africa with the Rwandan experience to provide for a showcase as a successful performer. Her Excellency, the Rwandan Minister of Foreign Affairs and International Cooperation delivered an eloquent speech focusing, among other things, on the yearning for post-conflict peace and reconciliation, revival of the age-old community values and practices as well as women's participation and empowerment in all aspects of national discourse.

No matter what local and external critics of the present Rwandan Government say, she reiterated that the policy being pursued by her country prioritizes more on poverty alleviation by first providing its citizens with 'bread and butter' rather than 'abstract democratic ideals' which have of little relevance in the advancement of their 'human dignity'. According to her, democracy has no universally applicable formula and thus should be used cautiously as it fits to each and every national realities prevailing on the ground.

Admittedly, the Minister did not blatantly deny that there are certain social elements that are, in one way or another, dissatisfied with the system of governance in her country. Yet, she agonizingly tried to convince the attendees that it is a matter of national interest and deliberate choice to maintain the system with all its impurities in an imperfect planet. Consequently, our logical interpretation of her ideologically-driven stereotype is that, for instance, the Rwandan Patriotic Front led by the current President Paul Kagame needs to ever remain in power, apparently for an indefinite period of time, regardless of its shrinking democratic credentials, so long as it is doing well in the promotion and championship of the country's social and economic development.

How controversial it is to think of what the Madam Minister wants to frame as 'economic development' in the conspicuous absence of a 'democratic atmosphere' and 'political pluralism'!!!

Often times, African colleagues, especially those in political power, unsuccessfully strive hard to detach democracy from development. After all, are development and democracy mutually exclusive? Would it not be possible to simultaneously develop both the economy and democracy? What does 'development' mean in the first place?

The UN General Assembly adopted a Declaration on the Right to Development in its Resolution No. 41 of 128 way back on December 4 1986. In that declaration, the term "development" has been defined as a comprehensive economic, social, cultural and political process, which aims at the constant improvement of the well-being of the entire population and of all individuals on the basis of their active, free and meaningful participation in development and in the fair distribution of benefits resulting there-from".

Moreover, the Vienna Declaration and Program of Action adopted by the World Conference on Human Rights in Vienna, Australia on June 25, 1993, establishes the inseparability and interdependence of all basic human rights and democratic freedoms, be they of civil, political, social, economic, or cultural origin. In fact, Art. 5. of the declaration proclaims that "All human rights are universal, indivisible, interdependent and interrelated". It goes on to elaborate that "the international community must treat human rights globally in a fair and equal manner, on the same footing and with the same emphasis". According to the declaration, "while the significance of national and regional particularities and various historical, cultural and religious backgrounds must be borne in mind, it is the natural duty of states, regardless of their political, economic and cultural systems, to promote and protect all human rights and fundamental freedoms" without unnecessarily prioritizing one over the other.

In the light of the above-mentioned provisions of international law, therefore, it makes no sense for any principled government of the day to be purportedly proud of its developmental achievements short of comparable records on the democratic front, as well. Without any doubt, Rwanda's astounding success in the areas of livelihood promotion, locally-engineered inter-group harmony and reconciliation, women's empowerment, militating corruption and its drive for clean cities is something that has to be praised and applauded by the rest of Africa.

Whether or not the republic is a 'developmental state' in an

**Often times, African colleagues, especially those in political power, unsuccessfully strive hard to detach democracy from development.**

ideologically driven categorization, it is up to our respective leaderships to follow the example of that tiny nation on those important parameters. Nevertheless, that alone does not ever guarantee the unshakable legitimacy and sustainable credibility of a healthy and capable regime as long as it is not also democratically organized on the basis of free, fair and periodically conducted general elections with constitutionally prescribed tenures and term limits.

While the public lecture was progressing, I had the privilege to raise a question on whether Rwanda, (a good friend of Ethiopia), was, in any way, justified to hold a public referendum on December 18, 2015 in a bid to get the approval of a constitutional amendment which Paul Kagame had initiated for no reason other than to potentially extend his presidential rule and thereby remain in power undisputed until 2037, amidst widespread criticism both at home and abroad. To my realistic expectation, however, the minister was clever enough to simply bypass the challenging question without any explanation or comments whatsoever.

Given her ministerial position virtually assumed by the will of the president, I don't personally blame Louise Mushikiwabo, for not reacting promptly to my challenging intervention. Due to the nature of our regimes with democratic deficits, I had to assure myself that any separate statement of indifference on her part likely to embarrass the government would perhaps entail undesirable consequences. What else could I have done, had I put myself in her shoes?

***Note:***
Art. 101 of the original 2003 Rwandan Constitution (as amended first in 2010) imposes two term limits for the Office of the Presidency. The length of each term of office lasts 7 years. In accordance with this normative prescription, President Paul Kagame is currently in his second term which shall have expired in 2024, after which he would be barred from standing as a lawful candidate.

It is in an effort to do away with this prohibitive obstacle that the above-cited constitutional article has deliberately been amended as of December 24 2015 thus reducing the term length from 7 to 5 years, in which case he will be qualified to compete afresh for the third term following the completion of his effective rule in 2024. Should that happen, therefore, he is more likely to remain in power for additional ten years until 2034.

**Ato Merhatsidk Mekonnen is a senior expert in Law as well as Peace and Security Studies. Currently, he is serving in the capacity of a Chief Legal Advisor to the President of the Amhara National Regional State, Ethiopia. He can be reached at: clickmerha1@gmail.com**

# “እማ”

ታምሩ ከፈለኝ (የሻረግ) 2ኛ አመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል

www.facebook.Com/ደቀ ከፈለኝ ወየሻረግ

ቀኑ ይህ ቀን ነበር አስታውሰዋለሁ

በርጋታ ጉዞዬ ሁሉን እየቃኘሁ

ቆንጆ ልቤን ሰርቃው መንገድ ቆሜ ቀረሁ

ያንን አጋጣሚ እንዴት ረሳዋለሁ

እስኪ ልመልስሽ በትዝታ ይገፍሽ

አይንሽን እያሁ አይናይኔን እያየ. . .

ከተንቀሳቃሽ ስልኩ ጋር ተያይዞ፤ በቲሸርቱ ውስጥ አልፎ ጆሮው ላይ በተሰካው ቀጭን ገመድ ውስጥ የሚንቆረቆረው ሙዚቃ ትኩረቱን ሁሉ ይዞበታል፡፡

አጠገቡ ያሉ ተማሪዎች የሚሰሩት ጨንቋቸው የነገ ሂዎታቸውን ብሩህ የሚያደርጉበትን የትምህርት አይነት ለመምረጥ ሲጣደፉ እርሱ መሃላቸው ተቀምጦ ያለጭንቀት ሙዚቃውን ያዳምጣል፡፡

ገና ዩኒቨርሲቲ ሲገባ ምን እንደሚያጠና ያውቃል፤ ትንሽ ያስፈራው ዉጤቱ ነበር. . . . ለመረጠው የትምህርት አይነት ባይመጥንስ? አሁን ግን ስጋቱ አልፏል፤ ጭንቀት የለም፣ ስጋት የለም፣ ውጤቱ የመረጠውን እንደሚያስገኘው አምኗል፡ ፡ ጆፌ፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኦዲትርየም አዳራሽ የተሰበሰቡ ተማሪዎች አሁንም መረጋጋት ተስኗቸው ይዋከባሉ፤ ካንዱ ወደ ሌላው ይጣደፋሉ፡፡ የተወሰኑት ተቀምጠው የሚነገረውን ያደምጣሉ፡፡

ጆፌ ከፊት በኩል በቅርቡ ከተዋወቀው የዶርሙ ልጅ ጋር ተቀምጧል፡፡ የዶርሙ ልጅ በጆፌ ላይ አሻግሮ የሚመለከታቸው ኮረዶች ጆፌን አላሳሰቡትም፡፡ ትኩረቱ ሙሉ ለሙሉ በቀጭኑ ገመድ አልፎ እሚመጣው ሙዚቃ ላይ ነው፡፡

ለማን በዬ ባዶነት ለሞላው

ለማን በዬ ለገለባው ክብሬ

ለማን ብዬ ካበደው ጋር ልበድ

ለማን ብዬ ካጠፋው አብሬ

ለማን ብዬ እልህ ጠጋብቼ

ለማን ብዬ ቸካኝ ልሁን መራራቴን ትቼ. . .

በቅርቡ ለአድማጭ የደረሰው የአብነት አጎናፍር ዜማ ነው

የዶርሙ ልጅ ጆፌን መጎትጎት ጀመረ፤.

”ቺኮቹ እኮ እያዩህ ነው፡፡ አብሶ የመሃለኛዋ ተመስጣብሃለች፡፡”

“ባክህ ተወኝ የራሷ ጉዳይ. . . ሙዚቃዬን ላዳምትበት”

“ኧረ ይደብራል. . . ሙዚቃ ምናምን ትላለህ እንዴ? ቢያነስ ጎንህ ያለችውን እትት በላት እንጂ!

“አልበረደኝማ! እንዴት እትት ልበል!?

“አቦ አቶግማ!?” የዶርሙ ልጅ ተበሳጨ

”ከፈለክ ቦታ ልቀይርህ?” በጁ ሳይቀር እያመለከተው ለመነሳት ሲቃጣ ”ኧረ ተወው ፂሜን በላ ቀልቤን ብትገፈውስ? ህ!”

“በቃ ተዋ!” ጆፌ ወደ ጆሮው የሚገባውን ሙዚቃ ከፍ አድርጎ ከሙዚቀኛው ጋር መዝፈን ጀመረ

ያሆ በል ጃሌ

ያሆ በል ምነው

ያሆ በል ጆፌ

ያላወቀህ ማነው

ጓደኛው ተቅበጠበጠ፡፡ ጆፌ ያላያቸውን ኮረዶች እየተመለከተ ምራቁን ዋጠ፡፡ ብዙ አሰበ፤ ብዙ ተመኘ፡፡ ከጎኑ ወደ ተቀመተው ጆፌ አይኑን አነጣጠረ፡፡ በልቡ ሰደበው፡፡ “ፉራ!”

ጆፌ የተቀመጠበትን ወንበር መደገፊያ በጀርባው ሙጥኝ ብሎ፤ጭንቅላቱን መደገፊያው አናት ላይ አስደግፎ ወ ጆሮው የሚሰርገውን ሙዚቃ ይኮመኩማል፡፡

ደሞ ሊመጣ ነው ያ ዘመን

ትዝታ ድርቦ እየጠራረገ

መቀበል ነው እንጂ የመጣውን ሁሉ

መች ይደበቁታል ዐልፈልግም ቢሉ

ጆፌ ወደ ጆሮው እየሰረገ ያለውን ሙዚቃ ያለፈ ትዝታውን ቀሰቀሰበት፡፡ ወደ ኋላ ብዙ ነጎደ፡፡ የልጅነት ፍቅረኛውን . . . ስሟን ቄስ ይጥራውና ያቺን ከንቱ አውታወሰ፡፡ በልጅነት ልቡ ውስጥ ፍቅርን ዘርታ፣ ኮትኩታ አሳድጋ ሰብሏ ደርሶ ሲዘናፈል፤ አላጭድም፣ አልከምርም፣ አሎቃም፣ ምርቴን አልሰበስብም፣ ያለችውን የህፃንነት ልቡንለመከራ፤ አይኑን ለንባ የሰጠችውን ያቺን ከንቱ አስታወሰ፡፡

ከሷ በኋላ ሴት እርም ብሏል፡፡ “ፍቅሬም መውደዴም፤ መውደዴም ፍቅሬም የመፅሃፍ ገፆች ናቸው፡፡ ከግእዝ የፊደል ገበታ ውስጥ አምስተኛዋ የ”ሰ” ዘር “ሴ”ለመልካም ነገር አልተፈጠረጭም፡፡

ሴት

ሴጣን

ሴጋ

ሴራ

ሴሰኛ . . . እነዚህንና ሌሎች በርካታ መልካም ያልሆኑ ነገሮችን የዛለች እና” እያለ ይፈላሰፋል፡፡

የተሰበሰቡት ተማሪዎች አሁንም ይተራመሳሉ፡፡ humanity, sociel sience, educational and beheveiral sience የትኛውን የትምህርት ፋኩልቲ እንደሚመርጡ ጠቸግረዋል፡፡

የጆፌ ዶርም ልጅ ይቅበጠበጣል፤ ጆፌ ሙዚቓ ያዳምጣል፡፡

በድንገት ወደ ጆሮው እየሰረገ ካለው ሙዚቃ በዙ እጥፍ ያማረ ቃና ያለው የሳቅ ድምፅ ተሰማው፡፡ ጆፌ፡፡ ጆሮው ላይ የሰካውን ነቅሎ ወደ ግራው ዞረ፡፡ ሳቋ አላባራም፡፡ከሁለት ሴቶች ቀትሎ የተቀመጠቺው ልጅ ነበረች፡፡ ሳቂዋ፡፡

“ጥርሷ እንዴት አባቱ ነው የሚያምረው!?” ጆፌ ለራሱ ተናገረ”. . . ቆንጅዬ ልጅ ናት፡፡”

ከጆሮው ላይ የነቀለውን መልሶ ሰክቶ እንደቅድሙ ተቀመጠ፡፡ ብዙ ሳይቆይ የማያውቀው ሃይል ውስጡ ተፀንሶ ወደ ኋላ እንዲዞር ገፋፋው፡፡ አንገቱን ዞር ለሊያደርግ ሊል ሲል ልቡ ስለፈራ ተወው፡፡ ሃሳቡ ግን አልተረጋጋም፡፡ “ደግመህ እያት . . . አይዞህ አትፍራ!“ እያለ ወተወተው፡፡

“ለመ፣ንድነው የማያት?” ጆፌ ደነፋ

“አለማየት ስለማትችል ነዋ ጆፌ¡¡ ሃሃሃሃሃሃ ኧይ ጆፌ ጉድ ሆንሽ. . . ተነደፍሽ!” የራሱ ሃሳብ አላገጠበት፡፡

“ምንድነው የምነደፈው?” የበለጠ ጀግና ለመምሰል ሞከረ

“ተይ ተይ ጆፌ! በባዶ ሜዳ አትደንፊ!”

“አቦ ተወኝ፡፡”

ጆፌ ወደግራው ዞረ. . . ተመለከታት፡፡ እውነትም ቆንጆ ናት፤ ውብ፡፡

“አየህ ብዬህ ነበር እኮ እርሷን አለማዬት አ-ት-ች-ል-ም!”

“እና ማየት ብርቅ ነው እንዴ!? ማየት በኔ ተጀመረ? ብሽቅ!” አኮረፈ፡፡

“ብርቅ እንኳ አልነበረም. . . ላንተ ነው እንጂ ለዘመናት በርቆብህ የነበረው፡፡”

“በቃ ተወኝ ሙዚቃዬን ላዳምጥበት፡፡”

“ቂ ቂ ቂ. . . . ሙዚቃ!? . . . ድንቄም ሙዚቃ¡ የኛ አድማጭ¡”

ጆፌ በንዴት ጆሮው ላይ የሰካውን አስተካክሎ ተስተካክሎ ተቀመጠ፡፡ አይኑ ያለፍቃዱ ወደግራው ሰረቀ፡፡ እጁን ዘርግቶ ሊያቅፋት ወደደ፡፡ አልቻለም፡፡ በሷና በሱ መሃል ሁለት ሴቶች ተቀምጠዋል፡፡ በልቡ ሰደባቸው “ቀፋፎች”

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# አክሱም ደርሶ መልስ (የጉዞ ማስታወሻ)

በታምሩ ከፈለኝ(የሻረግ)

2ኛ አመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

www.facebook.com/ ደቀ ከፈለኝ ወየሻረግ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ሁለተኛ አመት ተማሪዎች ነን፡፡ በአመቱ ከምንወስዳቸው ትምህርቶች፣ "የኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ቅኝት" አንዱ ነው፡፡ ትምህርቱ ወደ አክሱም ጉዞ ስላለው ሁላችንም የጉዞውን ቀን በጉጉት እንጠብቀው ጀመር፡፡ አይደርስ የለ ቀኑ ደረሰ፡፡

ሚያዝያ17/2008 ዓ.ም ሁላችንም ተሰብስበን የጉዞ መኪናችንን እንጠብቃለን፡፡ በግምት2፡45 አካባቢ መኪናችን መጥታ ተሳፈርን፡፡ በነገራችን ላይ በሌላ መኪና ይሁን እንጂ ከኛ ጋር የሚጓዙ የፎክሎር ተማሪዎችም አሉ፡፡ ጉዞ ተጀመረ፡፡ ጉዟችንን ከመሃላችን ያሉ ዘፋን አዋቂዎችና ከመኪናው ቴፕ የሚወጡ ዘፈኖች አዋዙት፡፡

እንዲህ ተጉዘን የሆነ ደብረታቦር ከተማው ገባን፡፡ አንዳንዶቻችን "የታንጉት ሚስጢር" የተሰኘውን የብርሃኑ ዘሪሁንን መፅሃፍ አስታወስን፡፡ በመፅሃፉ ውስጥ ያሉት ደብተራ አክሊሉና አለቃ ጋረድ ተያይዘው ደብረታቦር ሲገቡ የአጤ ጤዎድሮስ ሰራዊት ደብረታቦርን አድምቆ እንደጠበቃቸው እኛንም ነዋሪዎቿ አደማምቀው ጠበቁን፡፡ ከመሃላችን የቴወድሮስ ሰራዊት የሰፈረበትን ቦታ ለማየት የጓጓም አይጠፋ፡፡ ከሃሳብ አልዘለለም እንጂ፡፡

ደብረታቦር ምሳችንን ለመብላት ስንወርድ ከተማዋን እንብርት አካባቢ ዞር ዞር ብለን ተመለከትን፡፡ በትንሽ እይታችን ላይ ላመን ጥርጣሬ ስናክል ከተማዋ እየሮጠች ያለች ከተማ ናት፡፡ ለከተማዋ መታሰቢያ ጥቂጥ ፎቶ ተነስተን ምሳችንን በልተን ጎዞ ቀጠልን፡፡

ትንሽ እንደተጓዝን ነፋስ መውጫ ደረስን፡፡ እዚህ ከተማ ላይ ስንደርስ በደራሲ አዳም ረታ የተፃፈው "ግራጫ ቃጭሎች"ና በደራሲ አንዳርጌ መስፍን የተፃፈው "ጥቁር ደም" "ደም በደም"ና ያለፈቃዳችን ወደ አእምሮኣችን ገቡ፡፡ ብዙዎቻችን በግራጫ ቃጭሎች ውስጥ ያለው መዝገቡን አሰብን፡፡ ሹፌራችን ላፍታ ቆም አድርጎልን መዝገቡ ሁሌ እየሄደ የሚቀመጥባት ጉብታላይ ብንቀምጥ ወደድን፡፡ ሙስጠፋ ሻይ ቤት ገብተን መዝገቡ አብዝቶ ይወደው የነበረውን እንቁላል ፍርፍር ብንበላ እርጎ ብንጎነጭ የምንፆም ደሞ ትኩስ ነገር ብንቀምስ ተመኘን፡፡ ጠጉራችን የተንጨባረረብን ዱባለ ጋር ሄደን ብንከረከም አንጠላም ነበር፡፡ አልሆነም፡፡ ጊዜ የለማ! ጉዟችን ቀጥሎ ወልድያ ገባን፡፡

በተራራ የተከበበችው ወልድያ ከተማ ሲመለከቷት አረህ ውስጥ የበቀለች ትመስላለች፡፡ ከተማው እንደገባን ወደ ቀኝ ታጥፈን ትንሽ የማይባል ጉዞ ከተጓዝን በኋላ ዩኒቨርሲቲው ገባን፡፡ መምጣታችን ቀደም ብሎ ስላልተነገራቸው ጥቂት ቢያንገራግሩም አልገፉንም፡፡ አሳደሩን፡፡

ጀምበርን ቀድመን ተነስተን ጉዟችንን ቀጠልን፡፡ ሰማዩን ካልነካሁ ሞቼ እገኛለሁ ብለው ከስራቸው በተኮለኮሉ ጓዶቻቸው የሚገለገሉ የሚመስሉትን የሰሜን ወሎ ተራሮችን አልፈን ከሰማይ የተሳሳሙ የሚመስሉ ተራሮች ያሉበት ትግራይ ክልል ገባን፡፡ አላማጣ ስንደርስ ቁርስ በልተን በርታ ካልን በኋላ ጉዟችን ቀጠለ፡፡ መቀሌ ገባን፡፡

መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ገብተን ስፍራ ስፍራችንን ከያዝን በኋላ የሰማእታትን ሃውልት ልናይ ወጣን፡፡ ቆም ያለች ድንጋይ ስናገኝ ፊት ለፊቱ ካሜራ አሶድረን ፎቶ መነሳት የለመደብን እኛ ሃውልቱ ስር እየቆምን ፎቶ ከተነሳን በኋላ ወደ ሙዚየሙ ገባን፡፡ ሙዚየሙ ውስጥ ህውሃት እንዴት፣ መቼ፣ በማን፣ ለምን እንደተመሰረተ፣ ዋና ዋና የትግሉን ቦታዎች፣ ከትግሉ በፊትና በትግሉ ጊዜ የነበሩ እንቅስቃሴዎችን ከበቂ ማብራሪያ ጋር በፎቶ ተመለከትን፡፡ ታጋዮች በትግሉ ወቅት ይገለገሉባቸው የነበሩትን ቁሳቁሶችም አየን፡፡ ቁሳቁሶቹ አንዳንዶቹ ትክክለኛዎቹ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ ለጉብኝት ተመሳስለው የተሰሩ እንደነበሩ አስጎብኛችን አልሸሸገንም፡፡

በዚህ ጉብኝት ሁላችንንም ያስገረመን ትግሉ በድል ከተጠናቀቀ በኋላ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊን ጨምሮ ሌሎች አመራሮችን አሳፍራ ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ስትበር መንገድ ላይ ከፍተኛ ችግር ገጥሟት የነበረችውንና ተከስክሳ ያን ሁሉ ደም መፋሰስ መና ልታስቀር፣ ያሁሉ መሰዋትነት የተከፈለበትን ትግል አፈር ድሜ ልታገባው የነበረችውን አውሮፕላን ባይናችን ማየታችን ነው፡፡ በተሳፋሪዎች ፀሎትና ባብራሪዎች ብርታት የተረፈችው አውሮፕላን በቅርቡ ከሱዳን መንግስት በስጦታ ተበርክታ እንደመጣችም አስጎብኛችን ነግሮናል፡፡ ድርጅቱን ለማቋቋም ሃየሎም አርኣያን ጨምሮ በሌሎች ስድስት አመራሮች የባንክ ዝርፊያ የተከናወነባትን መኪናም አይተናል፡፡

ቀኑም እየመሸ በመሄዱ፡፡ ጉብኝታችንም በመጠናቀቁ ወደ ማረፊያችን ገባን፡፡ የበረታን ከተማዋን ዞር ዞር ብለን ተመለከትን፡፡ ቢያይዋት ቢያይዋት የማትጠገብ ያሸበረቀ ሳሎን የምትመስለውን ከተማ ባንጠግባትም ጊዜ ስለገደበን ወደ ማረፊያችን ሄድን፡፡ በለሊት ተነስተን ወደ አክሱም ተጓዝን፡፡

ደራሲዎች "ፀሃይ ከተራሮች ግርጌ ስትወለድ. . ." ሲሉ ለውበት ብቻ ይመስለን እንዳልነበር ዛሬ ከትግራይ ተራሮች ጀርባ ፀሃይ ስትፈልቅ ባይናችን ስላየን አንዳች ግርምት ልባችንን ሰቀዞን ብዙዎቻችን የሞባይላችንን ካሜራ እያወጣን በፎቶ ልናስቀራት ሞከርን፡፡ ጉዟችን ቀጠለ፡፡

አስገራሚ ተራሮችን እያየንና በተለያዩ ዘፈኖች እየተወዛወዝን ተጉዘን አክሱም ገባን፡፡ በዕለቱ ምንም አይነት ጉብኝት እንደሌለ፤ ጉብኝቱ የሚጀምረው ጠዋት እንደሆነ በመምህራችን ተነግሮን አክሱም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ወደተዘጋጀልን ማረፊያ ገባን፡፡ ዝም ብሎ ተኝቶ ማደሩ ስላላስቻለንና እስከዚህም ስላልመሸ አብዛኞቻችን ዞር ዞር ብለን ለመመለስ ወጥተን እስክንችል ጎብኝተን ተመለስን ጎናችንን አሳረፍን፡፡

ሲነጋ ሃውልቱ የሚገኝበት ስፍራ ሄደን አስጎብኚ ከቀጠርን በኋላ ባስጎብኛችን እየተመራን የጴንጠልዮን ተራራን፣ የንጉስ ካሌብን ቤተ መንግስት፣ የንጉስ ኢዛናን የድንጋይ ላይ ፅሁፍ፣ የንግስት ሳባን ቤተ መንግስትና የመዋኛ ገንዳ፣ የአክሱም ሃውልቶችንና ሳንቲሞችን ጎበኘን፡፡

## የአቡነ ጴንጠልዮን ተራራ

ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ በሆኑት በአቡነ ጴንጠልዮን ስም የተሰየመው ይህ ተራራ ከትግራይ በስተ ምስራቅ ይገኛል፡፡ በ6ኛው መ/ክ/ዘ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ዘጠኙ ቅዱሳን ከነበራቸው አላማ ውስጥ የክርስትና ሀይማኖትን ማስፋፋት(ወንጌልን መስበክ፣ የገዳም ህይወትን ማስጀመርና ማስፋፋት)፣ ፊደሎቻችን አናባቢ ስላልነበራቸው ለነሱ አናባቢ ማበጀት ቀዳሚው ነበር፡፡ በቆይታቸውም በድንጋይ ላይ ይፃፉ የነበሩ ሃይማኖታዊ ፅሁፎችን ወደ ብራና ገለብጠዋል፣ በግሪክና በሳባ የተፃፉ የሃይማኖት ማስተማሪያ ፅሁፎችን ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል፡፡ ይህም ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እድገት ከፍተኛ አስጠዋፆ አድርጓል፡፡

በዚህ ተራራ ላይም ጥቂት የማይባሉ የድንጋይ ላይ ፀሁፎች ተገኝተዋል፡፡

## የካሌብ ቤተ መንግስት

ባስጎብኛችን እየተመራን ከፈራረሰው የአጤ ካሌብና የልጁ የአጤ ገብረመስቀል ቤተ መንግስት ስር ከመሬት በታች ወደተገነቡት ዋሻዎች ዘለቅን፡፡ በዋሻዎቹ ውስጥ የነገስታቱ ሚስጥራዊ እቃዎች ይቀመጡበት የነበረውን ስፍራ አየን፡፡ ግድግዳውም ላይ በዚህ ዘመን የቴምብላሮች ምልክት ነው የሚባለውን አበባ መሳይ ቅርፅ ያለውን ምልክት ተመለከትን፡፡

ጉብኝታችንን ጨርሰን ወደ መኪናችን ስንሄድ አንድ ላይን የሚያሳሳ ሕፃን በሚጢጢ እጆቹ ትናንሽ መስቀሎች ይዞ እንድንገዛው ይቁለጨለጭ ጀመር፡፡ አስተማሪያችንና አንድ ሁለት ተማሪዎች የያዛቸውን መስቀሎች ገዙት፡፡ በጉዟችን ላይ ቆም ባልን ቁጥር በመኪናችን መስኮት እጆቻቸውን እያሾለኩ "ዩ ቴን መኒ" የሚሉትን ህፃናት አስታወስንና "ምነው እነደዚህ ልጅ ስራ ቢያስለምዷቸው" አልን፡፡ እኛም አይደለም ቴን መኒ ድንቡሎ አላቀመስናቸውም፡፡ ከቻሉ ቢሰጡንም አንጠላም ነበር፡፡

## የንጉስ ኢዛና የድንጋይ ላይ ፅሁፎች

ሹፌራችንን አስጎብኛችን እየመራው ተጓዝንና አንድ የድንጋይ አጥር ወዳለው ደሳሳ ቤት ገባን፡፡ ቤቱ ውስጥ በ4ኛው መ/ክ/ዘ በንጉስ ኢዛና የተሰራው ይህ ድንጋይ የተገኘው በ1981ኣ/ም በሶስት ያካባቢው አርሶ አደሮች ነው፡፡ ይህ ድንጋይ በሳባ፣ በግሪክና በግእዝ ቋንቋ የተፃፈበት ሲሆን ፅሁፎቹ የሚያትቱት ስለ ንጉሱ ድል አድራጊነት ነው፡፡

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# "እማ" ...

ከገጽ 11 የዞረ

ቀፋፎች ባላቸው ላይ አሳልፎ አይኑን ቀብቅቦባታል፡፡ እሷ ደሞ ወደሱ አትመለከትም፡፡ ተናደደ፡፡ "ምናል አንዴ እንኳ ብታየኝ? ስሟ ማነው? ፍቅረኛ ይኖራት? አ. . .አ በፍፁም ፍቅረኛ ሊኖራት ኤችልም. . ." ደፍጋሚ አያት አታየውም፡፡ ከተቀመጠበት ሳይነሳ በልቡ ዙፋን ላይ አደላድሎ አስቀመጣት፡፡

በልቡ ዙፋን ላይ እሷን ሲያስቀምጥ አንብቦ ልቡ ላይ ካስቀመጠው አንድ ነገር አነሳ፡፡

`I belive in love in firste sight. Because I am loving my mom since I opened my eye`

ፍቅር በመጀመሪያ እይታ እንደሚይዝ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም እናቴን የወደድኳት ገና አይኔን ስከፍት ነውና፡፡ እንደማለት ነው፡፡

ጆፌ ለራሱ ማውራት ጀመረ "እውነት ነው፡፡ ፍቅር ከሆነ ፍቅር ነው፡፡ አንዴ ብጫ ቆማ ባየኋት እንጂ ስሟ እኔን አያስጨንቀኝ፡፡ ማንም ትባል፡፡ ግን ልክ እነደናቴ በመጀመሪያ እይታ ስለወደድኳት እናቴ ናት፡፡ እናም እማ ብዬ እጠራለሁ፡፡ እማ፡፡ እማዬ፡፡ እናቴ፡፡ ማማ፡፡ እማ ፍቅሬ፡፡ እማ!. . . እማ!!! እ. . . ማ፡፡"

ችንቀቱን እረሳ፡፡ ችግሩን እረሳ፡፡ ሁሉን ረስቶ አዲስ ህይወት ሊጀምር ወሰነ፡፡ፍቅር፡፡ መውደድ፡፡

ፍጣሪው ዳግመኛ ጉዳት እንዳያደርስበት በልቡ ጠማፀነው፡፡ "ለዘየኣምን ኩሉ ይትከሃል-ለሚያምን ሁሉ ይቻላል" የሚለውን ቅዱስ ቃል መፀሃፍ ቅዱስ ላይ ማንበቡን አስታወሰ፡፡ ተፅናና፡፡ "ካመንኩ ሁሉ ይቻለኛል፡፡ ጊዜው ቢረዝም እንኳ አገኛታለሁ፡፡" ብሎነ ራሱን አፅናና፡፡

ሙሉ ተስፋ ሰንቆ ጎኑ ካለችው ልጅ ጋር ጨዋታ ጀመረ፡፡ በጥቂት ጊዜ ተግባቡ፡፡ እይኑ እየሰረቀ እማውን ይመለከታል፡፡ አታይውም፡፡

እንድታየው ጓጓ፡፡ በልቡ ፀለየ፡፡ልቡ በፍራት እየራደች ተመለከታት፡፡ ተመለከተችው፡፡ አየችው፡፡ ልቡ በሃሴት ቦረቀች፡፡ጆሮው ውስት በሰካው ቀጭን ሽቦ ውስት አልፎ ከሚመጣው የአብነት አጎናፍር ዜማ ጋር ተባብራ ልቡ አዜመች. . . አቀነቀነች. . . ደ-ነ-ከ-ረ-ች፡፡

እንዴት ብሎ እንደሚነግርሽ

ቃላት ጠፋው ልቤ ሚልሽ

ባትጠብቂም ምላሽ ከኔ

ታውቂዋለሽ ምላሽ ከኔ. . .

# Do Students' Diets Meet ...

continued on page 7

The dining plans that students are allowed to dine daily are characterized by food items that are high in refined gains, beans and a small amount of *meat* (It is locally termed as '*therefore*', (for only three patties of meat are served); have short term calorific value and low nutrient density. The food environment is characterized by the absence of some foods such as poultry, fish, dairy products, fiber foods, vegetables and fruits at least once a week or two or in any season for that matter. The students' decisions about what to eat are currently made in a situation where students are not offered opportunities for choices based on their requirement and preferences. There is no guideline or standard for food services on the school canteens. Nutrition labelling is also not required on what is being served by the cafeterias. The grains and the beans in most services are made up of refined raw materials instead of being served as whole grains. My point is that some of those grains and beans should have been better served as whole grains rather than refined. Whole grains supply complex carbohydrates, which are burned off slowly throughout the day and provide fiber, which keeps you full and regulates the digestive system. Meat and beans; indeed, provide proteins and minerals, which keep hunger at bay and provide a longer-term fuel supply than simple starches. On the contrary, good sources of animal proteins like fish and poultry are not available in this meal plan. Although we know that a variety of fruits, vegetables and dairy products are important parts of any diet, they are also exempted from the students' meal plan except a tomato sauce on Wednesdays and Fridays. For example, fruits and vegetables supply essential *vitamins and minerals*, give the body plenty of water. Many digestive processes in our body require certain minerals and vitamins to function properly. Leafy greens in particular supply plenty of fiber, while fruits like orange and vegetables like carrots and sweet potatoes supply plenty of *Vitamin* A.

Dairy products also supply *calcium, other essential minerals* and some protein, and they can also be high in fat and sugar. A good meal plan may aim for dairy products per day, but should stick to skim low-fat versions. The recent scientific recommendation about sugar, saturated fat and salt is to avoid, cut down or reduce intakes for a healthy diet. However, the current intakes by the students on sugar, saturated fat and salt (iodized Vis a Vis non-iodized) in their diets are not known exactly, and hence I propose that their diets should be investigated.

In connection, the safety, functionality and palatability of the diet served can be risk factor for a student's poor health and productivity. Thus, I recommend that steps should be taken to improve the situation through evidence based scientific research. It is known from the literature and human experience that fruits and vegetables, dairy products, better protein sources from animals such as fish and poultry yield more nutrition than cow meats and beans.

Whole grains are more effective in meeting dietary guidelines than refined grains. Research and development activities and insights in nutrition intervention programs can help to fill the gap in the current situation and move to a better nutrition and better student health and productivity by ensuring improved nutrition and healthy diet as a top priority.

I claim that working together with various institutions; we can attain the ultimate goal of improving healthy diets in our university. To mention a few for student nutrition and health in university contexts some programs such as FRESH (Food Resources Education for Student Health), HACCP (Hazard Analysis and critical control point principle) for food handlers and AQUPONICS (Aquaculture integrated with hydroponics) in school garden can have high impact on changing the food environment and behaviour. In addition, FOOD FORTIFICTION and SUPPLMENTATION can be considered for some nutrients that cannot be made available naturally. Other efforts to improve the quality of foods in schools could be integrated with agricultural programs such as SCHOOL GARDENING PROGRAMS and GREEN HOUSES, SCHOOL LIVESTOCK PROGRAMS and FARM-TO-SCHOOL PROGRAMS, which link local farmers providing fresh locally grown produce to school food service cafeterias, are some intervention opportunities to prevent diseases related to diet, maintain health and increase productivity in university students.

On the whole, we expect our students to have general health; maintain a healthy weight, consume a balanced diet with fruits and vegetables more frequently and do some moderate physical activities as they continue to learn and study hard to become tomorrow's adults in a scientific society. We cannot just expect our students to be good in academics. People live on good food and good education not on good words! The right nutrition and healthy life style free of alcohol, smoking and drug abuse can have a profound impact on the students' health, ability to fight disease, grow, better learn and reach their full potential.

# አክሱም ደርሶ መልስ ...

ከገጽ 14 የዞረ

ፈላሲት" በሚል ግጥም ውስጥ

ጥበበኛ እጅሽ ይመስክር

ስንዴዋን ለብርሃንሽ የጋገረው

አለቷን ለምኩራብሽ የፈለጠው

ዋልካዋን ለሽክላሽ የቆፈረው. . .

ያለው ወዶ አይደለም፡፡ የሽክላና የሽመናን ስራ እጅግ ዘመናዊ በሆነ መልኩ ያጣድፉታል፡፡ ጉብኝታችንን እንደጨረስን ከተማዋን እየተመለከትን ቆየንና ወደ ማረፊያችን ገባን፡፡ ጠዋት ወደ ባሕር ዳር ስለምንሄድ ከተማዋን ለመሰናበት ተመልሰን የወጣንም ነበርን፡፡

ሲነጋ ቁርስ በልተን ተሳፈርን፡፡ ከጎንደር እንደወጣን እግረ መንገዳችንን የጉዛራን ቤተ መንግስት ጎበኘን፡፡ በአሁን ሰኣት እድሳት ላይ ያለው የጉዛራ ቤተ መንግስት ከፋሲል ግንብ በፊት በአጤ ሰርፀድንግል (ከ1556-1589 ዓ.ም) የተሰራ ነው፡፡

ፋሲል ቤተመንግስት ዲዛይን ከሱ እንደተኮረጀ የሚነገርለት ይህ ቤተ መንግስት ውስጡ ዛሬ ዛሬ እጅግ ዘመናዊ በሆኑ ቤቶች ውስጥ እና የባህር ማዶ ፊልሞች ላይ የምንመለከተው ዘመናዊ የቤት ማሞቂያ ምድጃ ውስጡ አለ፡፡ በተመሳሳይ ምድጃው በፋሲል ቤተ መንግስት ውስጥም አለ፡፡

ጉብኝታችንን ጨርሰን ወደመኪናችን ገብተን ጉዞ ስንጀምር የሁላችንም አእምሮ ተወጥሮ ስለነበር ጭብጨባና ዘፈኑ በመጠኑም ቢሆን ቀንሷል፡፡ ከዛ የስልጣኔ ማማ ወርደን የተፈጠፈጥነው መቼ ነው? "ማነበረ መሪው" አለ ገጣሚ ሃይለጊወርጊስ ማሞ፡፡ እውነቱን እኮ ነው ካለም ፊት ቀድመን ስንመራ እንዳልነበር የትኛው መሪ ነው የኋላ ደጀን ያረግን? ማነው ካለም ፊት ሆነን ስንመራ ቀኝ ኋላ ዙር ብሎ ያለም ጭራ ያደረገን?

ወደ ቀድሞ ገናናነታችን ለመመለስስ መፍትሄው ምንድነው? አጤ ቴዎድሮስ ያቅሙን ተፍጨርጭሮ ነበር፡፡ ንግስት ቪክቶርያ የላከችለት ሽጉጥ ውስጥ ያደፈጠ ሞት ቀደመው፡፡ አጤ ሚኒሊክም ዝም አላለም ነበር፡፡ ውስጡ ተደብቆ የኖረ ሞት ቀደመው፡፡ እኛስ? ነው ገጣሚ ሰሎሞን ሞገስ እንዳለው ቅርሶቻችን ሁሉ በዘመናችን ላይ ከሚመሰክሩ፣ ስንፍናችንን ከሚነግሩን ቅርሶቻችንን ሁሉ አውድመን ምንም ነበርን እንበል?

በነገራችን ላይ የወደቀው የአክሱም ሃውልት ሲቆም የኢትዮጵያ ትንሳኤ እነደሆነ የዮራቶራዱ ሚራዥ ተናግሯል፡፡ ታዲያ ለምንድነው አጠገቡ እየቆምን ፎቶ ከምንነሳ ሃውልቱን ልናነሳው የማንታገለው? ፈረንጆቹስ "ቅርሶቻችሁ ባለም ቅርስ መዝገብ ስለተመዘገቡ 'እምናቅ እኛ እንጂ የማታውቁ እናንተ' አተነኳቸውም" የሚሉን ያገራችን ትንሳኤ እውን እንዳይሆን ይሆን? ብዙዎቻችን እነዚህንና ሌሎች ጥያቄዎችን እያብላላን ነበር ባሕር ዳር የገባነው፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# አክሱም ደርሶ መልስ ...

ከገጽ 12 የዞረ

. . .ቁመቱ 2.50 ሜትር ወርዱ 1ሜትር በሆነው በፅሁፍ የተንቆጠቆጠው ሃውልት ላይ "ኢዛና ንጉሰ አክሱም፣ ሳባ፣ የሂምያር፣ የቤጃ፣ የሲያም፣ የሳልሂን፣ የራይዳንና የመርዌ(የካሱ) ንጉስ ድል አድራጊው የሚል ጦማር ሰፍሮበታል። . . . ይስማእከ ወርቁ። ዮራቶራድ(ዴርቶጋዳ 4)። 2006ኣ/ም) ዴርቶጋዳ ማተሚያ ድርጅት። 165

## የንግስት ሳባ ቤተ መንግስት

በጥንታዊው የንግስት ሳባ ቤተ መንግስት ፍርስራሽ ስር ስንደርስ ብዙዎቻችን ዮራቶራድ በተሰኘው ልቦለድ ውስጥ ዴር33 በለሊት አምጥታ ጥላቸው ስትመለስ ሚራዥና ኪራኮስ ያነጉበትን ሽጥ ፈልጎ ማግኘት አሰኝቶን ነበር። አልቻልንም። ግን እልፍኝ አስከልካይ ሳያንገራግረን ወደ ቤተ መንግስቱ ሰተት አልን።

ይህንን ቤተ መንግስት ፈረንሳዩ አርኪዎሎጂስት በ1966 ከቆፈረ በኋላ በ7ኛው መ/ክ/ዘ የነበሩ ምሁራን ሃብታሞች አልያም የንግስና ዝርያ ያላቸው ሰዎች መኖሪያ እንጂ የንግስት ሳባ ቤተመንግስት አይደለም ቢልም ያካባቢው ነዋሪዎችና ፕሮፌሰር ዚጋርት ደሞ የንግስት ሳባ ቤተመንግስት እንደሆነ ይናገራሉ። ፕሮፌሰሩ ቦታውን ባስቆፈሩበት ጊዜ ሁለት አጥንቶችን አግኝተው ነበር። በአጥንቶቹ ላይ በተካሄደ ጥናት የንግስት ሳባ ቤተመንግስት እንደሆነ አረጋግጠዋል።

ቤተመንግስቱ 53 ክፍሎች ያሉት ሲሆን የሚጠቁመውም ንግስት ሳባ 53ኛ የአክሱም ንግስት መሆኗን ነው። ክፍሎቹም ንግስቲቱ ገላዋን የምትታጠበበት "ሻወር ቤት"ና ኩሽናን ጨምሮ ለበርካታ አገልግሎት ይውሉ ነበር።

## የንግስት ሳባ የመዋኛ ገንዳ

ቦታው ጋር ስንደርስ አጠገባችን ያለውን አስጎብኚ እያየን በእዝነ ልቦናችን ሚራዥንና ኪራኮስን ያስጎበኛቸውን አውአሎም የተባለ አስጊብኚ መስማት ጀመርን። አወአሎምም "ይህ የንግስት ሳባ የመዋኛ ገንዳ የነበረ ነው። ስፋቱ መቶ ሜትር በሰላሳ አምስት ሜትር ሲሆን አምስት ሜትር ጥልቀት አለው። ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺ አመተ አለም ከአለት ተጠርቦ የተሰራ ሲሆን ማይ ሹም በመባል ይታወቃል። የሹም ውሃ ማለት ነው። ስያሜው ንግስት ሳባ ትታጠብበት ስለነበረ የተሰጠው ነው። በኣራተኛው መ/ክ/ዘ ክርስትና ሲገባ አብርሃና አፅብሃ የተጠመቁበት ቦታ ነው።" አለን። ይስማእከ ወርቁ። ዮራቶራድ(ዴርቶጋዳ4) (2006ኣ/ም) ዴርቶጋዳ ማተሚያ ድርጅት። 164

## የአክሱም ሃውልቶች

ንግስት ሳባ ቤተመንግስት ውስጥ ተሆኖ ፊትለፊት ከሚታየው ገቦደራ ከሚባል ተራራ ተፈልፍለው የመጡት ሃውልቶች እጅግ ግዙፍ ከመሆናቸው የተነሳ እዚህ(አሁን እቆሙበት ስፍራ) በምን ተጉዘው ደረሱ ያሰኛል። አስጎብኛችን እንዳወጋን ሃውልቶቹ መጡ ተብሎ የሚታመንባቸው መንገዶች በርካታ ናቸው። የመጀመሪያው በዝሆን ተጭነው መጡ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ድንጋዮችን እያንከባለሉ አመጡት የሚል ነው። ሙዚየም ውስጥ ያየነው ስእል ደሞ በዝሆን ተጭነው መምጣታቸውን ያረጋግጣል።

ካሉት በርካታ ሃውልቶች መካከል ትልልቆቹ ሶስቱ ሲሆኑ ከሁሉም ትልቁ ደሞ የወደቀው ሃውልት ነው። አስጎብኛችን 520ቶን አካባቢ እንደሚመዝን ነግሮናል። አውአሎም ደሞ ለነ ሚራዥ 550ቶን እንደሚመዝን አውግቷቸዋል።

ከቆሙት ሁለቱ ትልልቅ ሃውልቶች ውስጥ አንድኛው ሮም ሄዶ የተመለሰው ሲሆን ወገቡ ላይ ተሰብሮ ቢታከምም ያለምንም ድጋፍ ቀጥ ብሎ ቆሟል። ሁለተኛው ግን ዙሪያውን ብረት ተወጥሮለት ወገቡን ተደግፏል። እኛ ግን እስሩ እየተኮለኮልን ፎቶ ከመነሳት ያገደን አልነበረም።

በነገራችን ላይ ሃውልቶቹ ላይ ያሉ የተለያዩ ቅርፆች ትርጓሜ እስካሁን አልተደረሰበትም።

እነዚህ ሃውልቶች በዘመናችን ላሉ በርካታ ስነፅሁፎች አስኳል ናቸው ማለት ይቻላል። በርካታ ደራሲያን ከሮም የተመለሰውን ሃውልትና የወደቀውን ሃውልት እያነፃፀሩ ፅፈዋል። ምሳሌ ዳንኤል ክብረት የሁለት ሃውልቶች ወግ በሚለው መፅሃፍ ውስጥ እንዲሁም ገጣሚ አበባው መላኩ ከራዲዮን በሚል የግጥም መድበሉ ውስጥ እነዚህ ሀውልቶች ርዕሰ ጉዳያቸው አድርገዋል።

## የአክሱም ሳንቲሞች

የተለያዩ የታሪክ መዛግብት እንደሚያስረዱት የአክሱም ሳንቲሞች የታተሙት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ3ኛው እስከ 7ኛው መ/ክ/ዘ ነው። በመጀመሪያ የታተሙት ሳንቲሞች መግለጫቸው የተፃፈው በግሪክኛ ሲሆን ከአጤ ካሌብ ዘመን በኋላ የታተሙት ሳንቲሞች መግለጫ የተፃፈው ደሞ በግእዝኛ ነው።

የእለቱ ጉብኝታችን ስላለቀ ወደ ማረፊያችን ተመለስን። ደክሞን ስለነበር አብዛኞቻችን ተኛን። ሲነጋ ወደ አክሱም ፂዮን ማርያም ቤተክርስቲያን ተጓዝን። ቤተክርስቲያን ስር እየቆምን ፎቶ ከተቀጨቀጭን በኋላ ወደሙዚየሙ ገባን። ሙዚየሙ ውስጥ የድንጋይ ላይ ፅሁፎችን፣ በወርቅ የተለበዱ መፅሃፍትን፣ የብር ከበሮዎችን፣ በወርቅ የተንቆጠቆጡ ካባወችን፣ የአጤ ዮሃንስን ጠጉር ከነ ወርቅ ወለባው ወዘተ አይተን ወጣን። ወደ ቤተክርስቲያኗ ቅኔ ማህሌትም ገብተን ጎበኘን፤ ፎቶም ተነሳንና ወጣን።

በርላይ መስቀል ላይ ስም እየፃፉ የሚሸጡ ሰዎች ከበቡን። ሁላችንም ማለት እስኪቻል ከኛ አልፎ ለዘመዶቻችንና ለጓደኞቻችን ሳይቀር ስማቸውን እያስቀረፅን መስቀል ገዛንላቸው። በቀጣዩም ቀን እዚሁ እንደምንችል ስለተነገረን ቀጠሮ እየያዝን ሄድን።

በማግስቱ ያልጠገብናቸውን ስፍራዎች ስንጎበኝና የምንሸማምተውን ስንሸማምት ዋልንና ለማለዳ ጉዞ ተሰናዳን። ጠዋት ወደ ዩኒቨርሲቲያችን መመለስ እንጀምራለን። የመንመለሰው ደሞ በመጣንበት መንገድ ሳይሆን በጎንደር ነው።

ሲነጋ አክሱምን ተሰናብተን ወደ ጎንደር ጉዞ ጀመርን። ነፋሱ እራሱ እሳት አዝሎ የሚሮጥ በሚመስለውን የሁመራ በረሃ አቋርጠን ተጉዘን ጎንደር ገባን። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ያዘጋጀልንን ማረፊያ ተቀብለን ጉብኝቱ ጠዋት ስለሆነ ዞር ዞር ብለን ተመልሰን ተኛን። ነግቶ ፋሲል ግምብ ጋር ሄደን አስጎብኚ ከያዝን በኂ ባስጎብኛችን እየተመራን ደብረ ብርሃን ስላሴን፣ ቁስቋም ማርያምን፣ የፋሲልን ቤተ መንግስትና የመዋኛ ገንዳ ጎበኘን።

## ደብረ ብርሃን ስላሴ

. . .በአድያም ሰገድ እያሱ የተተከለው የደብረብርሃን ስላሴ ትላልቅ ከሚባሉት የጎንደር አድባራት አንዱ ነው። ግቢው ሰፊ አጥሩ ሙሉ ግንብ ነው። ክብ ቅርፅ ካላቸው የጎንደር ቤተክርስቲያኞች ተለይቶ አራት ማእዘን የሆነው የደብረ ብርሃን ስላሴ ህንፃ የተገነባው በጭቃ ሳይሆን እንደ ፋሲለደስና ሌሎቹ ግንቦች በልዩ ኖራ ነው። . . . ብርሃኑ ዘርይሁን። የታንጉት ሚስጢር። (1979ኣ/ም)-186

የይስማእከ ወርቁ ድርሰት በሆነው ራህማቶሃራ(ዴርቶጋዳ2) ላይ ያሉትን አባባ ደጋጎን ተከትለው የገቡትን ፕሮፌሰር ባርናባስን ተከትለን ወደ ቅኔ ማህሌቱ ገባን። ውስጡ በተለያዩ ስእሎች አሸብርቋል። ስእሎቹ ብዙ ሺ አመት ቢያስቆጥሩም ውበታቸው ግን ንክች አላለም። አስጎብኛችን የስእሎቹን ትርጓሜ ሳይቀር እየተነተነ አስረዳን።

## ቁስቋም ማርያም

የታንጉት ምስጢሯ እማማ ደብሬ ታንጉትን ድንገት ከቤቷ አስወጥተው ጎንደርን ሲያስጎበኟት አንዱ መዳረሻቸው ይቺ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። እነትዬ ደብሬ ጥሻውን ወጥተው ቤተክርስቲያኑ ውስጥ አረፍ እንዳሉ እማማ ደብሬ ለታንጉት እንዲህ አሏት። ቁስቋም ማርያምን የተከሏትና ይህንን ግንብ የሰሩትማ እቴጌ ምንትዋብ ናቸው። መልካቸው ውብ፣ ጠባያቸው ውብ፣ እንዲያው እጁን ታጥቦ የፈጠራቸው ነበሩ ይባላል። እስቲ ይታይሽ! ዛሬ እንኳን ሴቱ ወንዱ እንዲህ አስቦ ይሰራል? ዛዲያ ብዙ ጊዜ እየመጡ ሱባኤ እየገቡ ተዚህ ነበር አሉ የሚቀመጡት። ብርሃኑ ዘርይሁን። የታንጉት ምስጢር። (1979ኣ/ም)-52

## የፋሲል ግንብ

እማማ ደብሬ የፋሲል ግንብን ለታንጉት ሲያስጎበኙ እንዲህ ነበር ያሏት። የኸ ደሞ የፃዲቁ ዮሃንስ ግንብ ነው። ደግሞ ፍቅር ግንብ ይሉታል።ምህኛቱን አልደረስኩበትም። አጤ ዮሃንስ እንደሆኑ ሰሌን ራሳቸው ሰርተው እየሸጡ ይኖሩ ስለነበር ስለፍቅር ማወቃቸውን እጠራጠራለሁ. . . ለዚህ አይደል ፃዲቁ የተባሉትስ።

የአድያም ሰገድ ኢያሱ ግንብ፣ የአፅራር ሰገድ ዳዊት ግንብ- ዘፈን ይወዱ ነበር ይባላል፣ የመሲህ ሰገድ በካፋ ግንብ፣ የቋረኛው እያሱ ግንብ፣ የራስ ጊዮርጊስ ግንብ. . . ብለው ዘረዘሩላት። ብርሃኑ ዘርይሁን። የታንጉት ምስጢር። (1979ኣ/ም)-51

እኛም ባስጎብኛችን እየተመራን ወደ ፋሲል ቤተመንግስት እየገባን ሳለ በሩጋር ስንደርስ "በነገራችን ላይ. . ." የሚል የአንዷት ጓደኛችንን ድምፅ ሰምተን ወደሷ ዞርን። የሁላችንንም አትኩሮት እንዳገኘች ስታረጋግጥ ንግግሯን ደገመችው። "በነገራችን ላይ. . ." ሁላችንም ምን ልትል ነው ብለን አሰፍስፈን እየተበቅናት ነው። ድምጧ የሆነ የምታውቀው የተለየ ነገር እንዳለ ይናገራል። ቀጠለች ". . . አፄ ፋሲል ስለ ጎንደር ብቻ አይደለም ስለ ጎጃምም ዘፍኗል" በመጀመሪያ ቀልድ መስሎኝ ነበርና ባጉል ሰኣት በመቀለዷ ተናደድኩ። ግን የእውነቷን እየተናገረች እንደሆነ ሲገባኝ በጣም ሳኩ። የሁላችንም ስሜት ነበር። አስተማሪያችን እንዳይሰማ ብፈልግም የሰማ ግን ይመስለኛል። ግን ምንም የታሪክ እውቀታችን እስከዚህም ቢሆን("እስከዚህም" የሚለው ቃል ራሱ ይበዛል) በአጤ ፋሲልና በፋሲል ደሞዝ መካከል ያለው ልዩነት ሊጠፋብን አይገባም ነበር። ለዚያውም የማህበረሰብ ሳይንስ ተማሪዎች ሆነን። በነገሩ አንዳንዶቻችን ተሳስቀን ሌሎቻችን እየተሳለቅንባት የቀረነው እያነቆርናት ወደ ግቢ ገባን። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ግን ራሷን ለመከላከል መከራከር እየሞከረች ነበር።

ግቢውስጥ ያሉትን ከላይ የተዘረዘሩትን ስድስት ግንቦች ጎበኘን። የሁሉም ግንብ አሰራር አስገራሚ ነው። ግንቦቹ ያሉበት ግቢ ዙርያውን 12 በሮች ያሉት ሲሆን የበሮቹ ስያሜም የሚከተሉት ናቸው። ጃን ተከል በር(ፊት በር)፣ወንበር በር(ሳራ ሳንባ)፣ አዛዥ ጠቋሬ በር፣አደናግር በር፣ እልፍኝ በር፣እምቢልታ በር፣ እርግብ በር፣ ባልደራስ በር፣ ቀጭን አሸዋ በር፣ ራስ በር፣ እንኮዬ በርና ግምጃ ቤት በር።

## የፋሲል መዋኛ ገንዳ

ዛሬ ዛሬ በያመቱ የሚከበረው የጥምቀጥ በአል የሚከበርበት ከቀሃ ወንዝ ተጠልፎ በአጤ ፋሲለደስ የተሰራውን መዋኛ ገንዳ፣ የንጉሱን ፈረስ "የዞብልን" መቃብር ስንመለከት ታንጉትን እንደገረማት ሁሉ እኛም በግርምት እጃችንን አፋችን ላይ ጫንን። ከፋሲል ግንብ ሁለት ኪሎሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው በዚህ የመዋኛ ገንዳ ዙርያ ባለው የድንጋይ ካብ የበቀሉ የችብሃ ዛፎች ስር ላጥሩ ልዩ ውበት ሰጥተውታል። ጉብኝታችን ተጠናቆ ወደማረፊያችን ሄድን። በጉዞኣችን ስለ ዣን ተከል ዋርካ እያወራን ነበር። በዛ አካባቢ ከሚነገሩ ቃላዊ ግጥሞች አንዱ የሚከተለው ነው።

ዣን ተከል ዋርካ መሬት ከነካ
ወንዱ እንቢ እንቢ ሴቱ እንካ እንካ

በርግጥ ዋርካው ዝም ቢሉት እስካሁን መሬት ይነካ ነበር። ግን ከላይ ያለችውን ትንቢታዊ ግጥም ፍራቻ ዝቅ ባለ ቁጥር ጎንደሬው ይከረክመዋል አልፎ አልፎም የተለያዩ አጫጭር ዱላዎችን እየተከለ ሽቅብ ይመልሰዋል።

በማግስቱ ጠዋት ተነስተን ወደ ፈላሻ መንደር ተጓዝን። የፈላሻወቹን የጅ ስራዎች አየን። ለካ ይስማእከ ወርቁ በመጀመሪያው የግጥም መድበሉ "የወንድ ምጥ" ውስጥ ባለ "ተመየጢ

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

# '*DeroFengel*': How *Serious is it for Farmers?*

*Chalachew Tarekegne (PhD Candidate)*

While I was travelling through West Gojjam to collect data for my research project, I met with many farmers who have encountered with serious challenges, and they informed me particularly the most challenging problem facing farmers for a long time. Surprisingly, during our discussion about my thematic focus, they switched their attention now and then to their critical problem.

It is necessary to note that I found the problem worth investigating, which BDU and other research institutes need to strive to find solution on their maximum potential. They informed me that they lost more money from poultry production due to the disease, which is locally termed as '*DeroFengel'. Indeed,* I personally saw the devastating effect of the disease outbreak in the areas where I was moving.

It is noted that the agriculture extension package encourages farmers to diversify their farming practices in order to challenge the prevailing effects of climate change. In this project, farmers are provided with alternatives to sustain their livelihoods and family well-being through selling animals and their products when crop harvesting fails because of climate change effects. Unfortunately, however, according to farmers, this approach has been challenged to function well, at least, for the 2007/2008 E.C production year.

The information collected from farmers themselves revealed that: firstly, their production this year is seriously affected by the climate change. Secondly, their animals; for instance, hens, cocks, and chickens are ravaged by 'DeroFengel'. Embarrassingly, it is reported that they are bewildered by both the effects of climate change and diseases related to animal health; in this case, '*DeroFengel'.*

In my opinion, therefore, this pressing problem didn't get much attention from researchers and rural development services providers. In a similar vein; however, attention is given to climate change and its associated impacts on smallholders' livelihoods. I am not an expert to say much more on animal health and diseases. However, like any responsible citizen, I would like to suggest that BDU has to really reach out the community by establishing a research centre with a standardized laboratory. It also needs to set up qualified human resources to solve such age-old pressing problem of the farming community.

Having finished collecting the data needed to my research, I was curious to find out observable evidence to determine if the problem really exists. Surprisingly, a group of farmers took me to a ditch where the carcasses were thrown. I took only some photos of the destroyed poultry so that you can make sense of it. Realizing the total devastating effect on the lives of the farmers, I think it was shocking to see the huge dead bodies of hens elsewhere ravaged by 'Dero Fengel'.

Specialists in the field might have done so much works related to such a disease. Yet, as far as the problem continues and farmers are still lamenting for help,I think there is a need to conduct further research on this grave problem!And, it must be food for thought for researchers in the field!



**Figure**. Effects of '*DeroFengel'* on Assets of Farmers' Livelihood

# ህልም እልም (ክፍል 4)

በቤተልሄም ሃይለማርያም 2ኛ አመት የኢኮኖሚክስ ተማሪ
www.Facebook.com/Bethelhem Hailemariam

ሲነጋ ማድረግ ያልባትን ደጋግማ እያጠነጠነች ባለችበት እንቅልፍ ሽለብ አደረጋት . . . በሩ ተንኳኳ:: ኳ..ኳ.. ደንግጣ ተነሳች:: ሌሊት ጋደም ብላ እንደነበረች ራሷን አገኘችው:: ሰአቷን አየች:: 12:15 በዚህ ሰአት ማን ሊመጣ ይችላል? መገመት አልቻለችም::

ኳ ኳ ኳ . . .

ጠጉሯን ወደኋላ ሰብስባ፤ በሌሊት ልብሷ ላይ ፎጣ ደርባ ወደ በሩ ተራመደች:: ከውጪ በኩል ሰላምታ ይሰማታል:: የሽማግሌ ድምፅ. . . ቀስ ብላ ከፈተችው:: "እእእእ. . . እንደምን አደርሽ እህተ ጊዎርጊስ ረበሽኩሽ እንዴ?" ያያቷ ንስሃ አባት መምሬ ጣሰው ናቸው::

"እንደምን አደሩ አባ" በጃቸው የያዙትን መስቀል ለመሳለም እያጎነበሰች::

"ከኪደነ ምህረት ኪዳን አድርሼ ስመጣ ፀበል ልርጫችሁ ብዬ ነው:: ያሽመግሌ አያትሽ እስካሁን አልተነሳም አይደል? አሁን አሁንማ ወደደጃፉም ደረስ ማለት ትቷል:: በስተርጅና ጎረመሰ መስል" አሉ የእድሜ ጥላ ያጠላበትን ጥርሳቸውን ፈገግ ለማድረግ እየሞከሩ::

"አአአአይ!" ምን እንደምትላቸው ግራ እየገባት "አሁን ካልጠፋ ቀን አያቴ ሲታሰር ጠብቀው ፀበል ሊረጩ ይመጣሉ? ነገረኛ ቄስ! እያለች ስታጉተመትም አላስተዋሏትም::

"በይ ገቢና ቀስቅሽው በዛውም አንድ ጆግ ውሃ ይዘሽ ነይ" ብለው ሳትጋብዛቸው ወደ መቀመጫው አመሩ:: እያመነታች ወደ ጓዳ ገባች:: ምን ብላ እንደምታሰረዳቸው ግራ ገበናት:: መቼም ታስሯል ብትል ነገሩን እንዴት እነደሚያከብዱት ታውቃለች::

ትንሽ ቆይታ ባዶዋን ተመለሰች "ምነው እህተ ጊዮርጊስ አሞታል እንዴ?" ባይኮሳተሩም የተኮሳተረ የሚመስል ፊታቸውን ጨምድደው ጠየቋት::

"አይ ማመም እንኳን አላመመውም:: ዘመድ ልጠይቅ ብሎ ገጠር ከሄደ ሶስት ቀኑ ነው::" አለች ውሸቷ እንዳይታወቅ ቃላቱን እያፈጠነች:: ዛሬ ባይሆንም ነገ ከነገ ወዲያ እውነቱን እንደሚያውቁ ብታውቅም ዛሬውኑ ተናግራ ከምታባብስ ይሻላል ብላ አስባ ነው::

"ምነው በሰላም? የዛሬ ሁለት ሳምንት አይደል እንዴ ጠይቋቸው የመጣው?"

"ወይጣጣ. . . ምነው አባ ደግሞ ሄዱል ሲባሉ እሺ ብለው ቢቀበሉ" አለች በሆዷ:: "አረ ችግር እንኳ የለም አንድ የዘመድ ልጅ ወልዳ እሷን 'እንኳን ማርያም ማረችሽ' ለበል ብሎ ነው::" አቤት የውሸቱ ፍጥነት ባንዴ ሰካካችው::

መምሬ ጣሰው ግን አልተዋጠላቸውም:: "ነፍሰ ጡር ዘመድ ነበረቻችሁ እንዴ? አልነገረኝም እኮ!" አጠያየቃቸው የነገር እንደሆነ ያስታውቃል::

"አይ አባ. . . እሱ እንዲህ አይነት ጨዋታ መች ትዝ ይለዋል ብለው ነው?"

"እሺ . . . እምምም. . . ይሁን:: ለማንኛውም ውሃውን አምጪውና ውዳሴ ማርያም አድርሼ አንቺን ረጭቼሽ ልሂድ:: መቼም እሱ የለም ተብሎ እንዲሁ አልመለስ::"

"አዎ ልክ ነዎት::" ተመልሳ ወደ ጓዳ እየገባች "አሁን ፀበል ተረጩ አልተረጩ ሰሞኑን ለፍታት መምጣትዎት አይቀር" አለች በልቧ ያደራችው የተንኮል ድር መፈፀሚያው ቅርብ እንደሆነ ተስፋ እያደረገች::

> "አሁን ፀበል ተረጩ አልተረጩ ሰሞኑን ለፍታት መምጣትዎት አይቀር" አለች በልቧ ያደራችው የተንኮል ድር መፈፀሚያው ቅርብ እንደሆነ ተስፋ እያደረገች::

"እህተ ጊዎርጊስ ማን ትባላለች የወለደችው ሴት" አሏት ከጓዳ ሳጥወጣ የሚንቀጠቀጥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው::

"ስሟን እንኳን አላውቀውም:: እኔ መች ዘመድ እግባባለሁ ብለው::" ውሃውን ከፊታቸው እያስቀመጠች መለሰችላቸው::

ወሬውን ተወት አድርገው ጉሮሯቸውን ጠረጉና ጋቢያቸውን ገለጥ አርገው በቀይ ጨርቅ የተጠቀለለች ለብዙ አመት አብራቸው የቆየች መዝገበ ፀሎታቸውን አውጥተው ንባባቸውን ጀመሩ:: ፎጣዋን እንደለበሰች ከፊት ለፊታቸው ቆማ ጎንበስ ቀና እያለች "አሜን" ማለቱን ተያያዘችው:: እሳቸው ሲያነቡ ከንፈሯን እያንቀሳቀሰች ትከተላቸዋለች:: አንዳንዴ ቀና እያሉ ይመለከቷታል:: ውስጧ አንዳች ሃሳብ እንደለ አልጠፋቸውም::

መምሬ ጣሰው የኤልሳን ቅልስልስነት አይወዱትም:: "ህህ. . . እባብም እኮ እየለሰለሰ ነው የሚነድፍ" ይላሉ ለአያቷ ባሽሙር:: ለነገሩ እሳቸውም ቢሆን ትሁት ለመምሰል የምትጥረው አመሏ ያናድዳቸዋል እንጂ የታዋቂ ሰው ነፍስ አባት መሆናቸው ውስጥ ውስጣቸውን ያኮራቸዋል:: መንገድ ላይ ላገኙት ሰው ሁሉ "አሁን እኮ ኤልሳቤት አያት ጋር ፀበል ረጭቼ መምጣጤ ነው" እያሉ ማውራት ያሰደስታቸዋል:: አንዳንዴ ግን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

